# በባህል ሕክምና ዕውቀት የሕመም መንስኤ እሳቤና መለከፊያ ዐዉዶች ትንተና በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ

ተመስገን በየነ አበጋዝ፣ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ኢሜል፡ temesgenb35@gmail.com

## አጠቃሎ

*ይህ ጥናት "በባህል ሕክምና ዕውቀት የሕመም መንስኤ እሳቤና መለከፊያ ዐውዶች ትንተና በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ" በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ ዐቢይ አላማ* በባህል ሕክምና ዕውቀት የሕመም መንስኤ እሳቤና መለከፊያ ዐውዶችን *መመርመር ነው። ጥናቱ፣ የሕመም መንስኤ እሳቤና መለከፊያ ዐውዶችን መግለጽ፤ በባህል ሕክምና ሂደት አዎንታዊና አሉታዊ ተግባራትን መጠቆም የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎችን አካቷል። እነዚህን ዝርዝር ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የመስክ መረጃዎች፤ በቃለመጠይቅ፣ በምልከታ፣ በቡድን ተኮር ውይይት እና በንጥል ጥናት ዘዴዎች ተሰብስበው፤ በማስታወሻ፣ በመቅረጸ ድምጽ፣ በፎቶና በቪዲዮ ካሜራ ተሰንደዋል። የመስክ መረጃ ሰጪዎች፤ የኦርቶዶክስ እምነት (98% የአካባቢውን/ነዋሪውን ማኅበረሰብ ይመለከታል) ተከታዮችን ብቻ ታላሚ በማድረግ (ከሶስት ወረዳዎች 76 ሰዎች) በዓላማ ተኮር እና በአጋዥ ጠቋሚ ናሙና ስልት ተመርጠዋል። ከዐብይና አጋዥ መረጃ ሰጪዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች፤ በይዘትና በምድብ ተደራጅተው፤ ዓይነታዊ የምርምር ይዘትን በመከተል በሥነ ዕውቀት (Epistemology) እና በማኅበራዊ ግንባታ (Social Constructionist theory)፣ ሕዝባዊ የሕመም መንስኤ ንድፈ ሃሳቦችን (Lay theories of illness Causation) መሰረት በማድረግ፤ ከተፈጥሮ ባሕርይ እና ከባህል-ተኮር ማብራሪያ ሞዴሎች አንፃር በመፈተሽ፤ በገላጭ፣ በይዘት ትንተና እና ትርጓሜ (Interpretation) ስልት ተተንትነው ቀርበዋል። በትንታኔው መሰረት በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ /በባህል ሐኪሞች/ እሳቤ፤ የሕመም መንስኤዎች ጅን፣ ዛር፣ ቡዳ፣ የመሬት እና የዐየር ጋኔል ተደርገው እንደሚታሰቡ ጥናቱ ይገልፃል። የሕመም መለከፊያ ዐውዶች፤ በሕሊና ተሰውረው፣ በዐየር ተበትነው የሚኖሩ ኢጋንንት፤ በዕፅዋት የሰፈሩ፣ በእንስሳት የሚበሩ ኢጋንንት፤ በቆሻሻ የሚኖሩ፣ በወንዝ የሰፈሩ ኢጋንንት፤ በደም፣ ምግብና መጠጥ የሚነሱ ኢጋንንት እንደሆኑ ጥናቱ አረጋግጧል። ብዙሃኑ* የባህል ሐኪሞች ከእምነት ተቋም የወጡ እና ለማኅበረሰቡ ቅርብና ተደራሽ መሆናቸው፤ ለሕሙማን ልማዱን በጠበቀ መልኩ ስነልቡናዊ ድጋፍ ማድረጋቸው፤ "በዝቅተኛ ወጪ" እና በውለታ አገልግሎት መስጠታቸው የሕክምና ሂደቱን ተመራጭ ቢያደርገውም፤ ከዘመኑ ሕክምና ልማድ፣ ከሕመም መንስኤ እሳቤና መለከፊያ ዐውዶች ጋር በተገናኘ ጉዳት እንደሚደርስ ጥናቱ ጠቁሟል። ይህን የባህል ሕክምና ዕውቀት ለማዘመን፤ በዘርፉ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመቅረፍ፣ እገዛ ለማድረግ እና የዘመናዊ ሕክምና አጋር እንዲሆን፤ የባህላዊና የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች ተቀራርበው ቢወያዩና ቢመካከሩ፣ በጋራ የሚሰሩበትን አጋጣሚ ቢያመቻቹ፤ ቀጣይ ውይይቶችና ጥናቶች ቢካሄዱ የተሻለ መሆኑን በመጠቆም ጥናቱ ተጠናቋል።

*ቁልፍ ቃላት፦* የባህል ሕክምና፣ የሕመም መንስኤ እሳቤ፣ መለከፊያ ዐዉዶች፣ ልማድ (እምነት)፣ የባህል ሐኪም፤

## መግቢያ

ይህ ጥናት በአማራ ክልል በደቡብ ጎንደር ዞን የሚካሄደውን *በባህል ሕክምና ዕውቀት የሕመም መንስኤ እሳቤና መለከፊያ ዐዉዶችን ተንትኗል። የዘርፉን ሕክምና* አበርክቶና ተግዳሮት መርምሯል። ደቡብ ጎንደር ዞን፤ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ ከሚገኙ 13 (አሥራ ሶስት) ዞኖች መካከል አንዱ ሲሆን የዞኑ ዋና ከተማ ደብረ ታቦር ነው። ደብረ ታቦር ከክልሉ ርዕሰ መዲና ባሕር ዳር በ98 ኪሎ ሜትር፣ ከአዲስ አበባ በ666 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። ደቡብ ጎንደር ዞን፤ በሰሜን ሰሜን ጎንደር፣ በደቡብ ምሥራቅ ጎጃም፣ በምሥራቅ ሰሜን ወሎ፣ በምዕራብ ምዕራብ ጎጃም፣ ጣና ሐይቅ እና

ምዕራብ ጎንደር ያዋስኑታል። ዞኑ በአስር ወረዳዎች እና በአምስት የከተማ አስተዳደር የተዋቀረ ሲሆን በ299 የገጠርና በ29 የከተማ በድምሩ በ328 ቀበሌዎች ተደራጅቷል። ይህ ጥናት በደቡብ ጎንደር ዞን ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል ፋርጣ (ደጋ)፣ ሊቦ ከምከም (ወይና ደጋ) እና እብናት (ቆላ) ወረጃዎችን በመለየት የመስክ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በነዚህ ወረዳዎች በአማካይ የኦርቶዶክስ (98%)፣ የእስልምና (1.5%) እና የሌላ እምነት ተከታዮች (0.5%) ይገኛሉ[1]።

የሰው ልጅ ጤንነቱን ለመጠበቅ፣ በሽታን ለመከላከል፣ ከአካባቢው ሥነምህዳር ሥርዓት (Ecological System) ጋር ለመላመድ፣ ከሕመም ለመፈወስና በሕይወት ለመኖር ሲል የራሱ የሆነ ታሪካዊና ባህላዊ የጤና አጠባበቅ ሥርዓት፣ ዕውቀት፣ በሽታን የመከላከልና የመፈወስ ስልት፣ ልማድ፣ ተግባርና ደንብ እንደነበረው፤ ምሁራን ጠቁመዋል (አሰፋ፣ 2008፤ Winkelman,2009; Molvaer 1987, P.11)[2]።

የኢትዮጵያን የባህል ሕክምና ዘርፍ ለሁለተኛ እና ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያነት በተለያየ መስክና ይዘት ያጠኑ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የሂዩማኒቲስ፣ የማኅበራዊ ሳይንስ፣ የስነ-ህይወት ሳይንስ ፋኩሊቲ ትምህርት ክፍሎች በዋናነት ይጠቀሳሉ። በሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተካሄዱ ቀደምት ጥናቶች ማዕከላዊ ትኩረት የባህል ሕክምና ተግባር፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ይዘትን፤ ማኅበራዊ ልማድና አመለካከትን፤ ሃይማኖታዊ እና እምነታዊ ተግባራትን፣ የባህል ሕክምና ጥበብ መተላለፊያ መንገዶችን ዳሰዋል (ዓለማየሁ፣ 2000፤ ምህረት፣ 2000፤ መስፍን፣ 2002፤ ተመስገን፣ 2003፤ ደነቁ፣ 2003፤ ፍቅርተ፣2009፤ ዐቢዩ፣ 2010)።

እንደ ዓለማየሁ (2000) ጥናት ግኝት የኑዌር ማኅበረሰብ ለበሽታ ያላቸው አመለካከት በዋናነት ከፈጣሪ እና ከሃገረሰባዊ እምነቶች ጋር የተያያዘ መሆኑን ያስረዳሉ። ምህረት (2000) ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ የባህል ሕክምና አገልግሎት በስፋት እንደሚሰጥ ጠቁመው፤ የባህል መድኃኒት ባለሙያዎች ዕውቀቱን በዋናነት ከሃይማኖታዊ ተቋማት እንደተማሩት ይገልጻሉ። መስፍንም (2002)፤ በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የባህል መድኃኒት ባለሙያዎች ለመድኃኒት ቅመማ የሚውሉ ግብዓቶችን ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት እና ከማዕድናት ቀምመው እና እምነታዊ ሥርዓቶችን ፈፅመው መድኃኒት እንደሚሰጡ፤ ተመስገን (2003)፤ በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች የባህል መድኃኒት ሲቀምሙ እምነታዊ ሥርዓቶችን እንደሚፈፅሙ፤ ደነቁም (2003)፤ በወላይታ ሶዶ ከተማና አካባቢዋ የዕፀ መድኃኒት ቅመማና

[1] የደቡብ ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ /ደ.ጎ.ዞ.ባ.ቱ.ቢ/፤ (2007፣ ገፅ 17-28)፤

[2]የፀሐፊው/ዋ ስም በእንግሊዘኛ ቋንቋ ከተፃፈ የአውሮፓውያንን የዘመን አቆጣጠር የሚያሳይ ሲሆን በአማርኛ ቋንቋ የተጻፈው ደግሞ የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር የሚያመለክት መሆኑን ልብ ይሏል።

አሰጣጥ ልማድ አካባቢ ተኮር ይዘትና ተግባር እንዳለው፤ ፍቅርተ (2009)፤ በከምባታ ብሔረሰብ ከዕፅዋት የሚገኙ ሃገረሰባዊ መድኃኒቶች አዘገጃጀትና አሰጣጥ አካባቢያዊ እምነትንና ግብዓትን ታሳቢ በማድረግ እንደሚከወን፤ ዐቢዩ (2010)፤ የቦሮ ሽናሻ ሃገረሰባዊ መድኃኒት ምንጩ፣ ተስተላልፎ እና ገቢር እየተዳከመ መምጣቱን፤ ማኅሌት (2011) ደግሞ በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ የሚተገበረው የሃገረሰባዊ መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ልማድ በጥቂት አዋቂዎች እጅ መገኘቱ፤ ከመንግስት አካላት ተገቢው ትኩረትና ዕውቅና አለማግኘቱ ሙያውን እያዳከመው እንደሄደ ገልፀዋል፡፡ ከአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ውጪ የተካሄዱ ቀደምት የጥናት ሥራዎች እንደየሙያ መስካቸው ቢለያዩም፤ የኢትዮጵያን የባህል ሕክምና ታሪክ፣ ልማድ እና ተግባር እንደሚከተለው ዳሰዋል፡፡

በታሪክ ትምህርት ክፍል (Assefa, 1992; አሰፋ፣ 2008)[3] የቀረቡ ጥናቶች፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰቱ የበሽታ ዓይነቶችንና የባህል ሕክምና ታሪክን ይዳስሳሉ፡፡ እንደ Assefa (1992) ጥናት ጥቁምታ፤ ቀደምት የባህል ሕክምና ተግባርና ምርምር በአባላዘር በሽታና ፈውስ ሥርዓት ላይ የተመሰረተ እንደነበር ጠቁመዋል፡፡ በተለይ በደሴ ከተማ አካባቢ የሚኖሩ መድኃኒት አዋቂዎች ለቁምጥና፣ ለቂጥኝ፣ ለኩፍኝ፣ ለጨብጥ፣ ለሳንባ ነቀርሳ ፈውስ፤ ከልማዳዊ ተግባር እና ከመንፈሳዊ ሥርዓት ጋር የተያያዘ ሕክምና ይሰጡ እንደነበር ገልጸዋል፡፡ ሁለተኛ ጥናታቸው "የኢትዮጵያ ባሕላዊ መድኃኒትና ሕክምና የምዕተ ዓመት ጉዞ" በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን የምርምራቸው ማዕከላዊ ይዘት የኢትዮጵያን የባህል ሕክምና ታሪክ፣ የመስኩን ባለሙያዎች ሕይወትና ልምድ፣ የዘመን ክስተት፣ የመንግሥት አዋጅና መመሪያን ይዘግባል (አሰፋ፣ 2008)፡፡ ከታሪክ ትምህርት ክፍል ባለፈ፤ በሥነ ሰብዕ ትምህርት ክፍል የባህል ሕክምና ልማድና ሥርዓትን የሚመለከቱ ይዘቶች እንደሚከተለው ተቃኝተዋል፡፡

በሥነ ሰብዕ ትምህርት ክፍል በባህል ሕክምና ዘርፍ ከተካሄዱ ጥናቶች መካከል በዋናነት Young (1970)[4], Mirgissa (1993), Abraraw (1998), Zerihun (2001), Wondwosen (2006) እና Tebaber (2015) ይጠቀሳሉ፡፡ የጥናቶቹ ትኩረት አካባቢያዊ ባህልን መሰረት በማድረግ በዘርፉ የሚሰጠውን ሕክምና፣ ተግባርና ሥርዓት ይገልፃሉ፡፡ Young (1970) የጥናታቸው ማዕከላዊ ጉዳይ በቤጌምድር የሚካሄደውን የባህል ሕክምና አምልኮና ተግባር በመዳሰስ፤ ውስጣዊና ውጫዊ የሕክምና (Internal and External) ዓይነቶችን፤ ተፈጥሯዊና መለኮታዊ የበሽታ መንስኤዎችን ለመከላከል፤ ማኅበረሰቡ በአስማትና በዕፀ መድኃኒት የሚፈውሱ

[3]Assefa, 1992 (MA)፤ አሰፋ፣2008 (PhD)፤ እነዚህ ጥናቶች በታሪክ ትምህርት ክፍል መስክ በአሰፋ ባልቻ (ዶ/ር) የቀረቡ ናቸው፡፡ በአማርኛና በእንግሊዝኛ የተፃፉበት ምክንያት የምርምር ሥራዎቹ መገኛ ቋንቋን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

[4]Young (1970) የኢትዮጵያን የባህል ሕክምና ያጠኑ የውጭ አገር የሥነ ሰብ ባለሙያ ናቸው፡፡

የባህል ሐኪሞችን እንደሚጠቀም አስረድተዋል። Mirgissa (1993) በኢሉባቦር የሚገኙ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች መንፈሳዊና ዓለማዊ በመባል በሁለት እንደሚከፈሉ ጠቁመው፤ በመንፈሳዊ ኃይል በመታገዝ ሕሙማንን ለመፈወስ የጫት መቃም ሥርዓት፣ ልመና፣ ጸሎትና ዱአ (Duai) እንደሚያካሄድ ጠቁመዋል። Abraraw (1998) ደግሞ በደሴ ከተማ ሰዎች የጤና እክል ሲገጥማቸው ሁለቱንም (መንፈሳዊ እና ዓለማዊ) የባህል ሕክምና ዓይነቶች በአማራጭነት እንደሚጠቀሙ፤ በአካባቢው ዘመናዊ ሕክምና የሚገኝ ቢሆንም አብዛኛው ማኅበረሰብ የባህል ሕክምና ዘርፍን እንደሚመርጥ፤ በጥናታቸው ገልፀዋል። Zerihun (2001) በዛይ ደሴት በሚገኙ የአዕምሮ ሕሙማን ላይ ጥናት አካሂደዋል። የአዕምሮ ሕመም መነሻ ከመንፈስ ጭንቀት፣ ከማኅበራዊ፣ ከኢኮኖሚ ቀውስ እና ከፖለቲካ አንጻር እንደሚከሰት አስረድተዋል። በጥናታቸው ግኝት ለአዕምሮ ሕሙማን የሚደረገው እንክብካቤና በማኅበረሰቡ ያለው አመለካከት ዝቅተኛ መሆኑን ጠቁመዋል። Wondwosen (2006)፤ በአዲስ አበባ የሚካሄደውን የባህልና የዘመናዊ ሕክምና ጥምረትና ሥርዓትን መርምረዋል። በጥናታቸው ይዘት የባህል ሕክምና ዘርፍ ውስብስብና እና የተለያዩ ተግባራትን ያካተተ መስክ መሆኑን ጠቁመው፤ ከዘመናዊ ሕክምና ጋር በመጣመርና በመተጋገዝ የማኅበረሰብን ጤና ማሻሻል እንደሚቻል አመላክተዋል።

በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ትምህርት ክፍል በባህል ሕክምና ዙሪያ ጥናት ያካሄዱ Mekonen W. (2008) እና Mekonen M. (2010) ይጠቀሳሉ። እንደ Mekonen W. (2008) ጥናት፤ የምዕራብ ጎጃም ዞን ማኅበረሰብ ለእብድ ዉሻ በሽታ ፈውስ ከዘመናዊ ሕክምና ይልቅ፤ የባህል ሕክምናን ምርጫቸው እንደሚያደርጉ አስረድተዋል። Mekonen M. (2010) ደግሞ፤ የኩናማ ማኅበረሰብን የባህል ሕክምና ሥርዓት እና ተግባር አጥንተዋል። አብዛኛው የኩናማ ማኅበረሰብ በሽታን ለመከላከል፤ ከሕመም ለመፈወስ የባህል መድኃኒቶችን በብዛት እንደሚጠቀሙ፤ በጥናታቸው አረጋግጠዋል።

የባህል ሕክምናን ከሣይንስና ከማኅበረሰብ ልማድ ጋር በማገናኘት፤ ከአጠኑ የሥነ ሕይወት ሣይንስ ትምህርት ክፍል Fekadu (2001) ይጠቀሳሉ። በጥናታቸው ሂደት፤ ለመድኃኒት የሚያገለግሉ ዕፅዋት በዘመናዊና በባህላዊ ሕክምና ዘርፍ ያላቸውን ሚና በመለየት፣ የዕፅዋቱን የመድኃኒት አቅምና የፈውስ ኃይል በቤተ ሙከራ በማረጋገጥ፣ በባህልና በዘመናዊ ሕክምና የሚሰጡትን ጠቀሜታዎች መጠቆማቸው፤ በዚህ ይዘት ከተጠቀሱ ጥናቶች የተለዩ ያደርጋቸዋል።

የማኅበረሰብን የባህል ሕክምና ሥርዓት፣ ዕውቀትና ልማድ ማጥናት አንዱ የፎክሎር መስክና ተግባር እንደሆነ ምሁራን ያስረዳሉ (Yoder, 1972, p. 192)። የባህል ሕክምና ዘርፍ፤ ከፎክሎር ጥናት መስኮች "ሃገረሰባዊ ልማድ" (Social Folk Customs) በሚል ምድብ ውስጥ የሚካተት ሲሆን በዚህ ንዑስ ክፍል "ሃገረሰባዊ መድኃኒት" (Folk Medicine) በዋናነት (Huffored, 1986, p. 307) ይጠቀሳል። ሃገረሰባዊ ሕክምና ደግሞ ተፈጥሯዊ (ኔቸራዊ/ዓለማዊ) መድኃኒትን "Natural (rational or secular) folk medicine" እና መለኮታዊ "Magi

co-religious (magic or spirituals)" ተግባራትን ያካትታል (Yoder, 1972, p. 192; Murdock, 1980, p. 6 እና ፈቃደ፣1991፣ ገጽ 13)። ከአካባቢያዊ ሥነ ምህዳር የሚገኙ ተፈጥሯዊ መድኃኒት ደግሞ እፅዋትን፣ እንስሳትን፣ አዕዋፍትን፣ ማዕድናትንና ነፍሳትን በመጠቀም የሚቀመም መድኃኒት ሲሆን በዘርፉ የሚሰጠውን የሕክምና ተግባር (Kokawaro, 1976; Konadu, 2007; Riddle, 2013) ያጠቃልላል። Hurreize (2006, p.120)፤ የባህል ህክምና በአንድ በኩል ፎክሎር በሌላ በኩል ደግሞ የሕክም ዘርፍ ሲሆን፤ መስኩ የባህልና የሳይንስ ትስስር፣ መስተጋብርና መሰል ጉዳዮችን አጣምሮ በመያዝ፤ የሁለቱን ግንኙነት በውል የሚያሳይ ሙያ እንደሆነ ጠቁመዋል።

የባህል ሕክምና ማለት ምን ማለት ነው? ሲባል Sofowora (1982, p. 2)፣ Black (1983)፣ Chavunduka (1994) እና WHO (2002; 2007)፤ የባህል ሕክምና ማለት የዕውቀት እና የተግባር አጠቃላይ ድምር (sum total) የሆነ፤ አካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ ማኅበራዊና አካባቢያዊ ጠንቆችንና ተውሳኮችን ለመከላከል፣ ለማስወገድና ለመመርመር ሲባል የሚተገበር፤ በተግባራዊ ልምምድ እና ምልከታ የሚከወን፤ ዕውቀቱና ጥበቡም በአብዛኛው ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ወይም በጽሑፍ እንደሚተላለፍ ገልጸዋል። በተመሳሳይ መልኩ Steiner (1986, p. 66)፣ (Good, 1987) እና Kannon (2004, p. 32) "የባህል መድኃኒት" ማለት የተለያዩ ብያኔዎች፣ ጽንሰ ሐሳቦች፣ የሥነ ምህዳር ዕውቀት፣ የማኅበረሰብ ልማድና ተመክሮዎች አጠቃላይ ድምር ውጤት ሲሆን፤ ከሥነ ምህዳር የሚገኙ ግብዓቶችን መሰረት በማድረግ ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት እና ከማዕድን ውጤቶች እንደሚዘጋጅ አስረድተዋል። በዚህ ጥናት፤ በባህል ሕክምና ዕውቀት የሕመም መንስኤ እሳቤና መለከፊያ ዐውዶች፣ የባህል ሕክምና ዘርፉ አዎንታዊና አሉታዊ ጉዳዮች ተተንትነው ቀርበዋል።

የጥናቱ ዐበይት አነሳሽ ምክንያቶች፤ ከባህል ሕክምና አንጻር፤ እንደMesseret (1996, p. 5) ገልፃ፤ "...አብዛኛው የገጠሩ ህዝብ በባህል መድኃኒትና በባህል ሐኪሞች ላይ ጥገኛ ነው፤ በከተማም ቢሆን ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ ተጠቃሚ ቢሆንም፤ በዘርፉ አጠቃቀምና አተገባበር ዙሪያ ሰፊ ምርምር አልተካሄደም" በማለት ይገልጻሉ። Agonafer (2004, p. 49) ደግሞ "... 90% የኢትዮጵያ ህዝብ የባህል መድኃኒት ተጠቃሚ ነው" ይላሉ። ቀደምት ጥናቶች በቀጣይነት ምን ይጠና (Research gap) ይላሉ? ሲባል (ተመስገን፣ 2003፤ ዐብዩ፣ 2010፤ Zerihun, 2001; Wondwosen, 2006; Tebaber, 2015)፤ ባህላዊ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሥርዓትና ተግባር በተለያዩ መስኮች የጥናት ትኩረት እንደነበር ጠቁመው፤ በባህል ሕክምና ዘርፍ እና ይዘት የሕመም መንስኤ እሳቤ፤ የመከሰቻ ዐውዶች፤ የበሽታ መለያ ስልቶች እና የምርመራ ዘዴዎች አፅንኦት ተሰጥቷቸው፤ በቀጣይነት ሰፊ ምርምር እንዲካሄድባቸው ምክረሃሳብ አቅርበዋል። እነዚህን የምርምር ክፍተቶች ታሳቢ በማድረግ እና በቀደምት ጥናቶች ያልተዳሰሱ ጉዳዮችን በመለየት፤ በባህል ሕክምና ዕውቀት ለሕመም መንስኤ የሚባሉ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው? በሽታ ከየት ይመጣል? የሕመም መከሰቻ ዐውዶች ምን ምን ናቸው? እሳቤው

እንዴት ይከወናል? በዘርፉ የሚከሰቱ አዎንታዊና አሉታዊ ጉዳዮች እንዴት ይተገበራሉ? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል።

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ በደቡብ ጎንደር ዞን የሚካሄደውን፤ የባህል ሕክምና ዕውቀት ከሕመም መንስኤ እሳቤና ከመለከፊያ ዐዉዶች አንጻር መመርመር ነበር። የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎችም፤ በባህል ሕክምና ዕውቀት የበሽታ መንስኤ እሳቤን መግለጽ፤ የመለከፊያ ዐዉዶችን ማብራራት ሲሆን በተጓዳኝ በባህል ሕክምና ሂደት የሚከሰቱ አዎንታዊና አሉታዊ ጉዳዮችን መጠቆም የሚሉ ናቸው።

የዚህ ጥናት የመጀመሪያው ፋይዳ፤ በዘርፉ የሚታዩ የምርምር ክፍተቶችን በመቃኘትና በመለየት፤ በባህል ሕክምና ዕውቀት የሕመም መንስኤ እሳቤና መለከፊያ ዐዉዶችን ለመገንዘብ፤ በዘርፉ የሚታዩ አዎንታዊና አሉታዊ ጉዳዮችን ለመለየት፤ የሕክምና ዘርፉን በውል ለመረዳት እና አበርክቶ ለማድረግ ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታሰባል። ከዚሁ በተጓዳኝ፤ ለጤና ፖሊሲ አውጭዎች፣ ለባህላዊ መድኃኒት አስተዳደር ቢሮ፣ ለብሔራዊ ዕፅዋት ማእከል፣ ለዘመናዊ ሕክምና ምርምር ማዕከል፣ ለባህላዊ መድኃኒት ጥናት ተቋም፣ ለቅድመ በሽታ ክትትልና ቁጥጥር ለሚያደርጉ ጤና ቢሮዎች፣ ለሕግ፣ መመሪያና ደንብ ለሚያወጡ አካላት፤ የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላል፤ ተብሎ ይታሰባል።

የዚህ ጥናት ወሰን፤ የተመራማሪውን ርዕስ፣ ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ ታሳቢ በማድረግ ከርዕሰ ጉዳይ፣ ከቦታ፣ ከጊዜና ከተጠኚ አካላት አንፃር ትኩረትና ገደቡን ወስኖ ተነስቷል። ከርዕሰ ጉዳይ አንፃር፤ ጥናቱ በደቡብ ጎንደር ዞን የሚካሄደው የባህል ሕክምና[5] ዕውቀት ከሕመም መንስኤና መለከፊያ ዐዉዶች አንጻር የሚመለከት ሲሆን በተጓዳኝ አዎንታዊና አሉታዊ የሕክምና ሁነቶች የጥናቱ ትኩረት ናቸው። ከጥናቱ ይዘትና ተግባር አንጻር የክርስትና እምነት ተከታዮችን (98%) ብቻ ትኩረት አድርጓል። የጥናቱ ውስንነት የሌሎች እምነት ተከታዮችን እሳቤና ተግባር በወካይነት ያላካተተ መሆኑን ልብ ይሏል። ስለሆነም ቀጣይ ተመራማሪዎች ክፍተቱን ቢሞሉ መልካም እንደሆነ ይታሰባል። የመስክ መረጃዎቹም ከባህላዊ ሐኪሞች፣ ከአካባቢው ማኅበረሰብ፣ ከታካሚና ከዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች አተያይ አንጻር ተሰብስበው ተተንትነዋል። ይህ ጥናት፤ የዘመናዊ ሕክምና የሕመም መንስኤ፤ የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎችን አይመለከትም፤ ለምን? ሲባል፤ ከዚህ ጥናት አላማና አድማስ ውጪ መሆናቸውን ልብ ይሏል።

## የጥናቱ ሥነዘዴ እና ንድፈ ሃሳቦች

ይህ ጥናት ከርዕሰ ጉዳይና ዓላማ አንጻር፣ ከሚሰበሰቡ የመስክ መረጃ አይነቶች፤ ከአተናተን ስልትና ይዘት፤ ጥናቱ አይነታዊ ምርምርን

[5] በአማራ ክልል በባህል ሕክምናው ዘርፍ ከሁለት ሺ (2000) በላይ የባህል ሐኪሞች እንደሚገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ (Wondosen, 2006, p. 44; Fekadu, 2001; Young, 1970)።

(Qualitative Research) ተግባራዊ አድርጓል፡፡ የመስክ በረጃዎችም በምድብ በምድብ ተደራጅተው፤ በገላጭ (Descriptive) እና በይዘት ትንተና (Content Analysis) ስልት ቀርበዋል፡፡ ጥናቱ ከቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ውስጥ፤ ቃለ መጠይቅ (Interview)፣ ምልከታ (Observation)፣ ተተኳሪ ቡድን ውይይት (Focus Group Discussion) እና ንጥል የጥናት (Case Study) ዘዴዎችን ተጠቅሟል (Shoemaker, 1990; Bauman, 1983, 1986; Geertz, 1973)፡፡ በሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶችና ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎች እንደአመቺነታቸው በቪዲዮ፣ በፎቶ ካሜራ፣ በቴፕና በማስታወሻ ደብተር ተጽፈዋል፤ ተቀርጸዋል፡፡ ይህ ጥናት በዓላማ ተኮር ስልት እና በአጋዥ ጠቋሚ ናሙና ስልት (Network or snowball sampling) መረጃ አቀባዮችን ለይቷል (Creswell, 2014; Dawson, 2009)፡፡ የመረጃ አቀባዮቹ ስብጥርም የሕክምና ልምድን፣ እድሜን፣ ማኅበራዊ ደረጃን፣ የስራ ባህርይን ያካተተ እንዲሆን ለማድረግ ተሞክሯል (Hammersley and Atkinson, 2007)፡፡

**ከቦታ እና ከናሙና (Sampling) አንጻር፡-** የደቡብ ጎንደር ዞን አካባቢያዊ መልክዓ ምድርን (ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላ ቦታዎችን) መነሻ በማድረግ ሶስት ወረዳዎች ተለይተው ምርምሩ ተካሂዷል፡፡ በሶስቱም ወረዳዎች 114 (በፋርጣ 43፣ በሊቦ ከምከም 34፣ በእብናት 37) ቀበሌዎች የሚገኙ ሲሆን፤ ለዚህ ጥናት መረጃ የሰጡ የባህል ሐኪሞች የሚገኙባቸው 16 ቀበሌዎች (ፋርጣ፣ 5፤ ሊቦ ከምከም፣ 6፤ እብናት፣ 5) የጥናቱ አባልና አካል ተደርገው ተካተዋል፡፡ ከእነዚህ ቀበሌዎች 27 የባህል ሐኪሞች፤ 9 የባህል መድኃኒት ተጠቃሚዎች፤ 3 የባህል ሕክምና ተጠቅመው የማያውቁ ግለሰቦች፤ 9 የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች፤ 19 የአካባቢው ማኅበረሰብ አባላት፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ሽማግሌና እናቶች፤ 4 የተፈጥሮ ሐብት ባለሙያዎች፣ 5 የዞንና የወረዳ ባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች፤ በድምሩ 76 መረጃ ሰጪዎች ተሳትፈዋል፡፡ የመረጃ ሰጪዎች እድሜ ከ24-95 ዓመት ባለው ክልል ውስጥ ይገኛል፡፡ ጥናቱ፤ የአካባቢውን ማኅበረሰብ ሃይማኖትና ብዛት ፣ አሰፋፈርና ተደራሽነት፣ የጥናቱ ተሳታፊና ታላሚ አባላትን (የባህል ሐኪሞችን) እንደ መነሻ ጉዳይ እና አስገዳጅ ሁነት በመውሰድ፤ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ላይ ብቻ (በአማካይ በሶስቱም ወረዳዎች 98% ይሸፍናል) ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

ጥናቱ በሶስት ንድፈ ሃሳብ ማሕቀፍ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ እነርሱም ሕዝባዊ የሕመም መንስኤ ንድፈ ሃሳቦች (Lay theories of illness causation)፤ የማንኛውም ሕመም መንስኤ፤ ከግለሰባዊ ተግባራት፣ ከማኅበራዊ ሕይወት፣ ከተፈጥሯዊ አካባቢና ከመለኮታዊ ኃይል እንደሚነሳ ምሁራን ያስረዳሉ (Murdock, 1980, pp. 8-12; Helman, 1984, pp. 72-73)፡፡ በዚህ ንድፈ ሃሳብ፤ የሕመም መንስኤዎች ምን ምን ናቸው? መከሰቻ ዐውዶች ምንድን ናቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

የማኅበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ (Social Constructionist Theory) ማዕከላዊ ይዘት፤ ዕውቀት ተፈጥሯዊ ሳይሆን ማኅበራዊ ውቅር ነው፡፡ በማኅበረሰብ መስተጋብራዊ ግንኙነት፣ በዐውዳዊ ሁነት፣ በግልና እና በጋራ ስምምነት የሚፈጠር፣ በግለሰቦች እና በማኅበረሰብ መዋቅራዊ አደረጃጀት የሚከወን፤

የጋራ መግባቢያ፣ ዕውቀት እና አመለካከት ላይ የተመሰረተ ተግባርን ይመለከታል። ዕውቀት በግለሰብ ደረጃ የሚመሰረት ቢሆንም ከግለሰብ ግለሰብ፣ ከማኅበረሰብ ማኅበረሰብ፣ ከተቋማት ሚና፣ ተግባርና እና አደረጃጀት አንጻር እንደሚለያይ፤ ዕውቀት ተፈጥሯዊ ሳይሆን ማኅበራዊ ስሪት (ውቅር) ነው። የሰው ልጅ የሚኖርበትን አካባቢና የዓለምን ምንነት፣ የክስተቶችን አመጣጥና ምክንያት ከልምዱ ተነስቶ የሚረዳበት ዘዴና ስልትን (Blaxter, Hughes and Tight, 2006; Sims and Stephens, 2005, p. 43, pp. 57-58; Kothari,2004; Berger and luckman, 1966, p. 1, pp. 65-77) ይመለከታል። በጥናቱ ሂደት፤ የማኅበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ እንዴት ይተገበራል? ሲባል፤ ማኅበረሰቡ (የባህል ሐኪሞች)፤ ለበሽታ መንስኤ ምን ዓይነት ማኅበራዊ እሳቤና መስተጋብራዊ ሕይወት አላቸው? እሳቤውን እንዴት አዳበሩት/ተገበሩት? ዕውቀትና ተግባሩ ግለሰባዊ እና/ወይም ቡድናዊ ስልት ይከተላል? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ቀርቧል።

ሥነ ዕውቀት (Epistemology)፡- የዕውቀት ጥናት ንድፈ ሃሳብ መሰረት የሚያደርገው በዕውቀት ምንነት፣ ተግባር፣ መዋቅር፣ መሰረት፣ ወሰን፣ አድማስ፣ ትክክለኛነት ላይ ሲሆን ይዘቱን በምክንያትና ውጤት ይመረምራል (Greco, 2001, pp. 117-119; Sosa, 2007, pp. 22-24)። ሥነ ዕውቀት፤ የሰው ልጅ የሚኖርበትን አካባቢና የዓለምን ምንነት፣ የክስተቶችን አመጣጥና ምክንያት የሚረዳበት ዘዴና ንድፈ ሃሳብ ሲሆን ተፈጥሮ እና አካባቢን ለመቆጣጠር፣ ለመመርመር እና ለማወቅ የሚደረግ ትግል፤ የማኅበራዊና ግለሰባዊ ፍላጎት እና ቁሳዊ ሐብትን ለማሟላት ሲባል ዕውቀትም እየሰፋ፣ እየዳበረ፣ እየተከማቸ ቅርፅ፣ ሥርዓትና ይዘት እያገኘ ይሄዳል (Greco, 2001, p. 118; ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት፣ 1978፣ ገጽ. 118)። ሥነ ዕውቀት፤ የዕውቀት አፈጣጠር መንስኤ፣ የድርጊት ስብስብና ሥርዓት ስደራ፣ ተፈጥሮ፣ አጋጣሚ፣ መጠነ ርዕይና አጠቃላይ መርሆዎች የሚያጠና የፍልስፍና ዘርፍ እንደሆነ ምሁራን ያስረዳሉ (ጠና፣ 2009፣ ገጽ 9፤ Denzin and Lincoln 2000, pp. 10-11)። Pietila (2003, pp. 3-4) ዕውቀትን በዋናነት ነባራዊና ኅሊናዊ በማለት በሁለት ይከፍላሉ። ነባራዊ ዕውቀት (Objective Knowledge) ይዘቱ በነባራዊ ዕውነታ፣ መረጃና ይዘት የሚወሰን፣ በተጨባጭ ምክንያትና ተግባር የሚረጋገጥና የሚገለፅ፣ ነባራዊ ዕውነታን በትክክል ለመረዳት፣ ማኅበራዊ መስተጋብርን ለማጤን፣ ተግባቦታዊ ሥርዓትን ለመገንዘብ፣ ማኅበረሰብ ተኮር ተግባራትን ለመመርመር የሚያገለግል ዕውቀት፤ እንደሆነ ይገልጻሉ።

በዚህ ጥናት፤ የሥነ ዕውቀት ንድፈ ሃሳብ እንዴት ተግባራዊ ሆነ? ሲባል የማኅበረሰቡን (የባህል ሐኪም፤ ታካሚ፤ የአካባቢውን ኗሪ) ዕውቀት፣ እሳቤ፣ ፍልስፍና፣ ምክንያታዊነት እና ተግባራትን ለመገንዘብ፤ ጭምቅ ሃሳብ እና አንኳር ርዕሰ ጉዳይ ለማውጣት፣ ሥነ ሕይወታዊና አካባቢያዊ ሣይንስን ለመረዳት፤… አገልግሏል። ማኅበረሰቡ ለበሽታና ለበሽታ መንስኤ ምን ዕውቀትና ፍልስፍና አላቸው? ለአካባቢያቸውና ዓለም ፍጥረት ምን ዓይነት እሳቤና ዕውቀት አላቸው? ሚታዊ ተረኮች እና የአምልኮ ሥርዓት በሽታ ከየት መጣ ይላሉ? አካባቢያዊ ዕውቀትና ተግባሩ እንዴት ይከወናል? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ቀርቧል።

## መረጃ ትንተና

በዚህ ንዑስ ይዘት ሥር የሕመም መንስኤ እሳቤና መለከፊያ ዐዉዶች፤ የባህል ሕክምና አዎንታዊና አሉታዊ ተግባራት እንደሚከተለው፤ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### የሕመም መንስኤ እሳቤ

በዚህ ንዑስ ይዘት ሥር የሕመም መንስኤ፣ የአጋንንት አይነትና መለያ ባሕርይ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

#### የሕመም መንስኤ

እንደ ደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ እሳቤና መረጃ፤ ለሕመም[6] መንስኤ "አጋንንት ወይም ርኩስ" መናፍስት ሲሆኑ፤ ዲያቢሎስ፣ ጋኔል፣ ጅን፣ ዛር፣ ቡዳ፣ ብሄሞት፤ በመባል ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ መናፍስት በዐየር፣ በዛፍ፣ በወንዝ፣ በተራራ፣ በባሕር እና በመሬት ተበትነው እና ተሰራጭተው ስለሚገኙ፤ የዐየር፣ የመሬት፣ የባሕር "ርኩስ"[7] መናፍስት ተብለው እንደሚጠሩ ይገልጻሉ፡፡

አስረጂ አንድ፡-

[7]በመስክ ቆይታዬ የባህል ሐኪሞች "በሽታ" ለሚለው ቃል "አጋንንት" የሚለውን አቻ ፍቺ ይመርጣሉ፡፡ የሕመም መንስኤ/የበሽታን ምንነት፣ ተግባርና ባሕርይ ለማስረዳትና ምላሽ ለመስጠት ሲጥሩ የመጨነቅ እና ግራ የመጋባት ስሜት ይታይባቸዋል፤ በአንጻሩ የሕመም መንስኤ/አጋንንት የሚል ጥያቄ ሲቀርብ አካላቸውን ዘና፣ ፊታቸውን ፈታ፣ ፈገግና ሳቅ በማለት የቀረበላቸውን ርዕሰ ጉዳይ በቀላሉ ይገልፃሉ፣ ያብራራሉ፣ ያስረዳሉ፡፡ በባህል ሕክምና አጋንንት ማለት "በሽታ" የሚለውን ቃል እንደሚተካ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች የባህል ሐኪሞች ጠቁመዋል፡፡ በዚህ ጥናት ይዘት እና ሂደት ውስጥ በሽታ እና ሕመም የትርጉም፣ የፍቺና የይዘት ለውጥ ሳይኖራቸው በአቻ ይዘት የቀረቡ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

[7]በዚህ ጥናት ይዘት ርኩስ መናፍስት፣ ሰይጣን፣ አጋንንት የሚሉ ቃላት ተመሳሳይ ይዘትና ፍቺ አላቸው፡፡ እንደ አመቺነታቸው በማፈራረቅ የተጠቀምኩ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

> *የአጋንንት ስምና ዓይነታቸውን ለማወቅ የመርበብተ ሰሎሞንን ድጋም [የአጋንንት ማስለፍለፊያና ማባረሪያ ፀሎት] እየተደገመ፤ ማነው ስማችሁ?... ስንት ናችሁ? እንዴት ያዛችኋት?... እየተባለ ሲጠየቅ፤… በታማሚዋ ላይ የሰፈረው መንፈስ ይናገራል። የአጋንንት፣ የጅን፣ የዛር መንፈስና ውላጅ [ከዛር የተወለደ/የዛር ልጅ ማለት ነው] መሆናቸውን ያጋልጣሉ፤ የት፣ መቼ እንደያዛት፣ በምን እንደያዛት ይለፈልፋል።… በማን ትለቃለህ? ዋስ ጥራ? ይባላል። ከመላእክት [ሚካኤል፤ ገብርኤል፣ አማኑኤል፣ ፋኑኤል፣] አንዱን ዋስ ይጠራል። … ሳይመለስ ይምላል፣ ይገዘታል፤ ወቶ ይሄዳል። በፀበል፣ በመስቀል እና በቃለ እግዚአብሔር ብቻ የሚለቅ አጋንንት አለ፤ ሌላው ደግሞ በማጨስ፣ በማሸተት፣ በማጠጣት፣ በጽፈት [በክታብ መልክ የተዘጋጀ የአጋንንት ማራቂያ ድግምት] አለ።… መንፈሱ ለቆ ሲሄድ ታማሚዋ ትነቃለች። ፀሎት ተደርጎ ድና ወደ ቤቷ ትሄዳለች።*

ከዚህ በላይ የቀረቡ የመስክ መረጃዎች እንደሚያስረዱት፤ የሕመም መንስኤ በዋናነት አጋንንት (ጋኔል) ሲሆኑ በሚበላ፣ በሚጠጣ፣ በሚሸተት፣ በሚለበስ፣ በሚታይ፣ በሚረገጥ እና በሚታሰብ [እኩይ ሥራ ለመተግበር] የሚዋረሱና የሚመጡ፤ አካላዊ ሥጋን በማድከም፣ አዕምሮን ሰላም በመንሳት፣ መንፈሳዊ ሕይወትን በማስተጓጎል፣ እኩይ ተግባራትን በማሳሰብና በማስፈጸም፣ ቀና መንገድን በማሳት፣ የማኅበረሰብ መተዳደሪያ ልማድን በመጣስ፤ ከዓለማዊና ከመንፈሳዊ የሕይወት መስተጋብር መነጠል፤ የአጋንንት ዐቢይ ሥራ፣ ሙያና ተግባር እንደሆነ በማኅበረሰቡ ይታመናል።

እንደ Pankhurst (1965; 1990; 2005) እና Helman (1984) ፤ የሕመም መንስኤ ንድፈ ሃሳቦች ይዘት፤ የሕመም መንስኤ መለኮታዊ ኃይል፣ ማኅበራዊ ሕይወት፣ ተፈጥሯዊ ዓለም እና ግለሰባዊ ባሕርይ እንደሆኑ ገልጸዋል። በዚህ ጥናት "ተፈጥሯዊ ዓለም እና ግለሰባዊ ባሕርይ" በማኅበረሰቡ አይጠቀሱም፤ የተፈጥሮ አደጋና ማዕበል ቢከሰት የፈጣሪ ቁጣ፣ በክፉ ሥራና ድርጊት የመላእክት ቅጣት ወይም የአጋንንት መቅሰፍት ተደርጎ ይቆጠራል። ግለሰባዊ ባሕርይም ቢሆን "ሰው ሲፈጠር እንደ ውኃ ንዑሕ ነው" ይባላል፤ በዚህ ዓለም ተግባር፣ ፍላጎትና ሥራ ነፍስ ትረክሳለች፣ ሃጢያት ትሰራለች፣ ሥጋዊ ባሕርይ የነፍስን ንጽሕና ያረክሳል፤ ተብሎ ይታሰባል። በግለሰቡ ላይ ያደሩ ርኩሳን መናፍስት "ጠጪ፣ አጫሽ፣ ዝሙት እንዲሰራ ምክንያት ናቸው"፤ ተብሎ ይታመናል።

በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ፤ የሕመም መንስኤ "በርኩስ" መንፈስ ተላላኪነት፤ የጻድቃን፣ የሰማዕታት እና የመላእክት ትዕዛዝ፣ መመሪያና ሕግን በመጣስ የሚመጣ ቅጣትና ቁጣንም ይመለከታል። አንድ ሰው በእባብ ድንገት ቢነደፍ "ፍርጃ ነው! የሰይጣን ወጥመድ ነው!" ይባላል። በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ በአገር፤ "እልቂት" ሲከሰት፣ ድርቅ ሲገባ፣ ርሃብ ሲነሳ፣ ሰው ሲሰደድ፤…

የፈጣሪ ቅጣት፣ የሃጢያት ብዛትና መንስኤ እንደሆነ፤ የፈጣሪን ቃል፣ ትዕዛዝና መመሪያ ባለማክበር፣ ለሕጉ አለመገዛት፣ በቃሉ አለመኖር፣ በሥርዓት አለመመራት፤ ያመጣው ቅጣት ተደርጎ በማኅበረሰቡ ይታመናል፡፡ መፍትሔው፤ መጾም፣ መጸለይ፣ መስገድ፣ ፈጣሪን መለመን፣ ምህረትና በረከት እንዲያወርድ መማጸን መሆኑን የሃይማኖት አባቶች መክረዋል፡፡


በአጠቃላይ የአጋንንትን መንስኤ ለመለየት፤ "ለመዋጋት እና ድል" ለመንሳት፤ ጾም፣ ጸሎት እና "ድጋም" በማድረስ የአጋንንቱን ባሕርይ፣ ምስና ግብር ለማወቅ፤ ማሰሪያ፣ ማናገሪያ፣ ማስለፍለፊያ፣ ማስወጫ፣ መገዘቻና ማባረሪያ ዕውቀት፣ ጥበብ እና ክህሎት ለማግኘት፤ አካባቢያቸውን ለመገንዘብና ምክንያታዊ ምላሽ ለመስጠት የባህል ሐኪሞች ጥረት እንደሚያደርጉ፤ ከመስክ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡ በቀጥይ ንዑስ ይዘት፤ የአጋንንት ዓይነትና መለያ ባሕርያት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡

### አጋንንት ዓይነት እና መለያ ባሕርይ

በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ እሳቤ፤ አጋንንት እንደሰማይ ከዋክብት እንደ ምድር አሸዋ በዐየር፣ በተራራ፣ በወንዝ፣ በመሬት ላይ ተበትነው እንደሚገኙ እና እንደሚኖሩ ይታሰባል፡፡ በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ፤ ለሕመም መንስኤ የሚባሉ የዛር፣ የጋኔል፣ የቡዳ እና የጅን ዘሮች… የአጋንንት ጭፍሮች እንደሆኑ ያታሰባል፡፡ ከእነዚህ ርኩስ መናፍስት ለመጠበቅ፣ ለመሰወር፣ ለመዳን፣ ለመፈወስ የባህል ሐኪሞችን[8]፣ የሃይማኖት አባቶችን፣ መጽሐፍ ገላጮችን፣ ስኒ አንባቢዎችን፣ ደጋሚዎችን፣ "በረድ ጣዮችን" ማማከር ዐቢይ ተግባር እንደሆነ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ Ben-Amos (1975; PP.165-166) ፤ የማኅበረሰቡን እሳቤ፣ ቀያዊ ምደባ፣ ትዕምርት፣ ክፍፍል እና እይታ መነሻ አድርጎ መመደብ እና በእነሱ አተያይ መተርጎም እንደሚገባ መክረዋል፡፡ ለሕመም መንስኤ የሚባሉ የአጋንንት ተላላኪ "አለቃና ጭፍሮች" ይዘትና ምድብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ የምድቡ ሥርዓት እና ይዘት የማኅበረሰቡን አከፋፈል፣ አተያይና እሳቤን መነሻ በማድረግ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

ምስል 1፡- *ለሕመም መንስኤ የሚባሉ ዋና ዋና የአጋንንት ምድብና የማኅበረሰብ ክፍፍል እሳቤ*

[8]በዚህ ይዘት የባህል ሐኪም ማለት፤ ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት፣ ከማዕድናት፣ ከነፍሳት፣ ከውኃማ አካላት የሚገኙ ግብዓቶችን በመጠቀም በመድኃኒት መልክና ይዘት ቀምመው ለታካሚ የሚሰጡ ባለሙያዎችን ይመለከታል፡፡




*ምንጭ፡- በጥናት አቅራቢው የተዘጋጀ መዋቅራዊ ምድብ ጥር/2011 ዓ.ም*

በዚህ ጥናት ዲያቢሎስ የአጋንንት አለቃ ሲሆን ዋና ዋና የሚባሉ የአጋንንት ዓይነትና ምድብ ጅን፣ ዛር፣ ቡዳ፣ የዐየር እና የምድር አጋንንት እንደሆኑ፤ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ የደቡብ ጎንደር ማኅበረሰብ በዕለት ውሎና አዳሩ፤ ለሕይወት፣ ለጤና እና ለበሽታ ምን ዓይነት እሳቤ አለው? ሕይወትን የሚሰጥ እና ጤናን የሚነሳ ማነው? ሲባል፤ የሕይወት ምንጭ ፈጣሪ፤ የሞት መንስኤ አጋንንት እንደሆኑ በማኅበረሰቡ ይታሰባል፡፡

## *የሕመም መንስኤ እና መለከፊያ ዐውዶች*

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር፤ ከሕመም መንስኤ እና "መለከፊያ" ዐውዶች (መንገዶች) መካከል፤ በሕሊና ተሰውረው፣ በዐየር ተበትነው የሚኖሩ አጋንንት፤ በዕፅዋት የሰፈሩ፣ በእንስሳት የሚበሩ አጋንንት፤ በቆሻሻ የሚኖሩ፣ በወንዝ የሰፈሩ አጋንንት፤ በደም፣ ምግብና መጠጥ የሚነሱ አጋንንት ይዘቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### በሕሊና ተሰውረው፤ በዐየር ተበትነው የሚኖሩ አጋንንት

በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ እሳቤ፤ የዛር መናፍስት በሰው ሕሊና በመሰወር፣ በመላው አካል በመሰራጨት መራቢያ አካልን በማድከም፤ ትዳር መከልከል፣ በሕልመ ሌሊት "መመታት"፣ ፈሪና ገርጋሪ ማድረግ፣ በጨለማ ማስቀመጥ፣ መደበትና የሕሊና መናወጥ፣ የፍላጎት መቀያየር እና ለብቻ ማልቀስ፤ የሕመሙ መንስኤ እና መለያ ምልክት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ለምሳሌ፡- "ቅጥቃጤ አደረብኝ! ሕልመ ሌሊት መታኝ! እባብና ዘንዶ ሲያባርረኝ አደረ፤ ዛር ሳትሆን አትቀርም፤ የቤት በር ወደ ጎን ሆናችሁ ክፈቱ፤ ቤት የዋለ ሰይጣን/መጋኛ እንዳይመታችሁ!..." ይባላል፡፡ ማኅበረሰቡ የዛር መንፈስ ምን ዓይነት ስሜትና ተግባር እንዳለው እንደሚከተለው በቃል ግጥም ይጠቁማል፡-

አይነቁም አይነቁም የሴት ዛር አይነቁም

እንደቀበኛ ላም ይገፋሉ በቁም፤...

ይባላል። የዛር መንፈስ አካልን ማንቀጥቀጥ፣ ማንገላታት፣ ስሜትን ማናወጥ፣ ቀስ በቀስ ሕሊናን የመሰወር ተግባርና ይዘት እንዳለው የቀረበው ቃል ግጥም ይጠቁማል። ሊቀጠበብት አብርሃም እና መሪጌታ ስዩም ዛር ማለት፤ ዘር፣ ነገድ፣ በዘር የሚወረስ፣ በዘር የሚመጣና የሚሄድ፤ በቤተሰብ ሲመለክ፣ ሲመረቅ፣ ሲገበር የቆየ ወደ ልጅ የሚተላለፍ፤ የቤት ጣጣና ልማድ መሆኑን ገልጸው፤ በባሕር፣ በዛፍና በተራራ የሚኖሩ ልቡሳነ ሥጋ (ሥጋ ለበስ አካል) የሆኑ፤ እንደሰው የሚዋለዱ፣ የሚበሉ፣ የሚጠጡ እና የሚሞቱ፤ ከሰው፣ ከእንስሳት፣ ከዛፍ፣ ከገደል፣ ከተራራ ተጠግተው እና ተሰውረው በመኖር የሚታወቁ፤ "የአጋንንት ዘር የጅን ዘመድ ናቸው" ተብሎ ይታሰባል። ደስታ (1962፣ ገጽ. 508) "ዛር" ማለት "ክፉ መንፈስ፣ ከግዜር ከመላእክት፣ የተለየ ውቃቢ፣... በሰው ላይ እያደረ ሰውን የሚያስጓራ የሚያስገዝፍ..." መንፈስ እንደሆነ ጠቁመዋል።

በባህል ሐኪሞች እሳቤና ገለጻ፤ የዛር መንፈስ ከቤተሰብ የሚወረስ፣ ከባሕርና ከየብስ በመነሳት ሰዎችን የሚለክፍ፣ "ቁራኛ" መንፈስ ተደርጎ ይቆጠራል። በማኅበረሰቡ እሳቤና እምነት፤ በዛር የተያዙ ሰዎች (ውቃቢ፣ ቃልቻ፣ ከራማ፣ አውሊያ በሚባሉ ቃላት ይጠራሉ) የመፍረድ፣ የመተንበይ፣ የመጠንቆል እና አጋንንትን የማናገር ኃይል እንዳላቸው ይታሰባል። የዛር መንፈስ ለጊዜውም ሆነ በዘላቂነት በሰው ሕሊና ላይ አርፎ አንደበታቸውን ቀይሮ እንደሚናገር ይታሰባል። ለመንፈሱ የሚስማማ፣ "ምስ" (ግብሩን) እና የደም መስዋዕት ካቀረቡ፤ ሥርዓቱን በወር እና በዓመት ከፈጸሙ ጠባቂያቸው፤ ሥርዓቱ ሲቀርና ሲጓደል ሕሊናቸውን ሰውሮ፣ አካላቸውን አጉድሎ፣ ሐብት ንብረታቸውን በትኖ ለሕመም መንስኤ፤ ለሞት ምክንያት እንደሆነ ይነገራል።

**አስረጂ አንድ፡- ሚት (Myth/Mythology) አዳኝ ወርቁ፡-**

> አዳኝ ወርቁ፤ መልካም መዓዛ፣ ሽቶ፣ እጣን፣ ወርቅና ጌጣጌጥ በብዛት ይወዳል። አካላዊ መልክ፣ ቁመና እና ደም ግባት ያላትን ሴት ከሌላ ወንድ አስቀድሞ ለራሱ ይመርጣታል። በዚህ ዛር የተለከፈች ሴት ማጌጥ፣ መኳኳል፣ መሽቀርቀር ታበዛለች፣ ወንድ ሲቀርባት ትርቃለች፣ በውበቷ ትመካለች፣ በእድሜ ዘመኗ ትዳር ሳታይ፣ ልጅ ሳትወልድ፣ ከርታታ ሆና ትቀራለች።... የአዳኝ ወርቁ ዛር መልክና ጠባይ የተዋረሳት ሴት፤ መኳኳል፣ በአንገቷ ወርቅ፣ በጆሮዋ ጌጥ ማንጠልጠል እና በፀጉሯ ማሰር

> ታበዛለች። በእግሯና በእጇ ላይ ጌጥ ታስራለች፤ የዛር መንፈሱ ልዩ ውበት እና ግርማ ሞገስ ይሰጣታል።… ብዙ ጊዜዋን ከወንድ ጋር አትሆንም፤ ቤት ዘግታ ትቀመጣለች፤ ውጭው ዓለም ያስፈራታል፣ ከቤተክርስቲያን ትርቃለች፤ ለመንፈሱ ቁራኛ ሆና ትኖራለች፤…

በማለት ይገልጻሉ። በባህል ሕክምና ዕውቀት፤ የዛር መንፈስ የአዕምሮ አካልን በመቆጣጠር፣ የሰውነት መራቢያ አካልን ማድከምና ሥርዓትን ማዛባት፤ ማኅበራዊ ኑሮን ማናጋት፤ ማኅበራዊ ሕይወትን ማቃወስ፤ ትዳር አልባ ማድረግና ማፍረስ፣ ልጆችን መበተን፣ ግለሰቡን ማስጨነቅ፣ ሥነ ልቡናዊ ጉዳት ማድረስ፤… የዛር መንፈስ ባሕርይና ተግባር ተደርጎ እንደሚታሰብ፤ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል።

በዐየር "ተበትነው እና ተሰውረው" የሚኖሩ የዐየር አጋንንት (ጋኔል) ይባላሉ። እነዚህ አጋንንት ለሰው፣ ለእንስሳት፣ ለዕፅዋት እና ለፍጡራን ዓለም (ሕይወት ለአላቸው) አስፈሪ፣ አስቸጋሪ፤ ከያዙ የማይለቁ፣ ከዐየር የሚወረወሩ፣ ታማሚን የሚያንገላቱ፣ "ቁራኛ" እና የእድሜ ልክ ሕመም፣ አብረው የሚያድጉና የሚኖሩ የዕድሜ ልክ መከራ፤ "ክፉ" መቅሰፍት ተደርገው ይቆጠራሉ። እንደመሪጌታ ስዩም መረጃ፤ በዐየር የሚኖሩ አጋንንት ለሰው ብቻ ሳይሆን ለፍጥረት ዓለሙ መቅሰፍት እንደሆኑ ጠቁመው፤ "የምድር ጋኔል ማር እንደ ነካ እጅ ይቆጠራሉ፤ የዐየር ጋኔል ደግሞ ቅቤ እንደነካ እጅ ቶሎ አይለቁም" ተብሎ ይታሰባል።

በአጠቃላይ በባህል ሕክምና እሳቤና ዕውቀት፤ "የስንፈተ ወሲብ" መንስኤ በዋናነት በዛር፤ የዐየር ጋኔል ደግሞ በፀሐይ ጨረር፣ በዐየር መጋጨት፣ "በብርድ ሕመም"፣ በድንገት መውደቅ፣ ጠጥቶ መስከር እና ደም መፍሰስ፣ በር ሲከፈትና ሲዘጋ በሚከሰት አጋጣሚ፤… የአዕምሮ ሕመም፣ የአካል መሽማቀቅ፣ የፊት መጣመም ይከሰታል፤ ተብሎ ይታመናል።

## በዕፅዋት የሰፈሩ፣ በእንስሳት የሚበሩ አጋንንት

በዚህ ጥናት ተተኳሪ ማኅበረሰብ እምነትና እሳቤ፤ የተወሰኑ ዕፅዋትና እንስሳትን የዛር፣ የቆሌ፣ የሰይጣን፣ የቡዳና የአጋንንት መኖሪያና መስፈሪያ ቦታዎች ተደርገው ይቆጠራሉ። የአጋንንት ማደሪያ የሚባሉ፤ ዕፅዋትን ከአካባቢያቸው ያርቃሉ፤ ከግቢያቸው ይነቅላሉ፤ በተመሳሳይ መልኩ ከእንስሳት ዓይነት የአጋንንት ተሸካሚ የሚባሉትን፤ ከቤታቸው ማራቅ፤ ወደ ግለሰብ እንዳይቀርቡ፣ እንዳይነካኩ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። በአንጻሩ ከአጋንንት ይጠብቃሉ፤ ከሰይጣን ይከላከላሉ፣ ከቡዳ መንፈስ ይሰውራሉ፤ ይፈውሳሉ የሚሏቸውን ዕፅዋትና እንስሳት በማቅረብ፤

*ዕፅዋትን በግቢያቸው ይተክላሉ፤ እንስሳትን ያረባሉ። ለምሳሌ፡- "ዕፀ ልባዊ/ት የአጋንንት ሰራዊት መኖሪያ፤ ዋርካ የዛር መንፍስ ማደሪያ፤ ዋንዛ የሰይጣን መከለያ (በመብረቅ ያስመታል)፣ ሾላ ጋኔል ይጠራል፣ ማንጎ አባወራ ይገፋል፤... ጅብ አጋንንት ተሸክሞ ይዞራል፤... እባብ የሰይጣን ውላጅ ነው፤..." ይባላል።*

*ከነዚህ ይዘቶች መካከል ከዕፅዋት፤ ዕፀ ልባዊት፣ ዋርካ፣ ሾላ፣ ዋንዛ፣ ማንጎ፤... ከእንስሳት፤ ሥጋ በል የሆኑ (ጅብ፣ እባብ፣ ዘንዶ፣ ጥቁር ሙጨጭላ ወይም "ፋደት/ሽለምጥማጥ" ዘር)፤... በማኅበረሰቡ ይፈራሉ። ከነዚህ ዕፅዋትና እንስሳት በተቃራኒ፤ ከዕፅዋት ዓይነት ጌሾ፣ ብሳና፣ ግራዋ፣ ሎሚ፣ የቅመማ ቅመም ዘር በሙሉ፤... ከእንስሳት ሣርና ቅጠል የሚበሉ እንስሳትን ያቀርባሉ። ለምን ያርቃሉ/ያቀርባሉ? ለሚሉ ጥያቄዎች እንደሚከተለው፤ ከማኅበረሰቡ እሳቤና ተግባር አንፃር ምላሽ ቀርቧል። በማኅበረሰቡ እምነትና እሳቤ የአጋንንት ማረፊያና መስፈሪያ፤ ቡዳ የሚያሲዙ፣ ጋኔል የሚያስመቱ ተብለው ከሚፈሩ ዕፅዋት መካከል የዕፀ ልባዊ/ት ትረካ እንደሚከተለው ቀርቧል።*

አስረጂ ሁለት፡- **ሚት (Myth/Mythology)፤ *ዕፀ* ልባዊ/ት (*ገፀ* ሰብእ)፡-**


> *ዕፀ ልባዊ/ት በቆላና በወይና ደጋ አካባቢ የምትገኝ፤ ከሣር ወይም ከችፍርግ ወገን የምትመደብ፤ አበቃቀልና ዕድገቷ እንደ ካሮት ነው።... በዕጿ ሥር ገፀ ሰብዕ የመሰለ፤ ትዕምርተ ተባዕትና ትዕምርተ ዕንስት ምልክት አላት። በግንድና ቅጠሏ አካል ላይ እንደ ሰው፤ የእጅ መዳፍ እና አምስት የጣት ምልክት አላት። ዕጿ፤ አርባ አራት የአጋንንት ጠባቂ ሰራዊት የሰፈሩባት፣ የቡዳ እና የዛር መንፈስ ተሸካሚ ናት። ...በተለይ አነስታይ የሆነችው ዕፀ ልባዊ/ት ወር በገባ በሃያ ዘጠነኛው ቀን የወር አበባ ታያለች።...ይህም፤ የሒዋን መርገምት ተምሳሌት ነው፤ ዕዳዋን እየከፈለች ነው። ...በሃያ ዘጠነኛው ቀን ቀረበው ሲመለከቷት በቅጠሏና በስሯ መጋጠሚያ ቦታ በግንዷ ዙሪያና ቀለበት ክርክር ላይ ደም ይፈሳታል፣ ታዣለች፤ ከሌላው ቀን በተለየ የምድር ቁጫጭና የጉንዳን ሰራዊት ግንዷንና ቅጠሏን ወረው፤ የሚፈሰውን ደም ይልሳሉ። ...የዕጿን መልክ፣ ዓይነትና ባሕርይ የማይለይ ሰው በእጁ ቆርጦ ቢቀምሳት ቡዳ ታደርጋለች፣ ጋኔል ታስመታለች፣ አዕምሮን ትሰውራለች፤... የዛር መንፈስ አሲዛ ዛፍ ላይ ትሰቅላለች፣ ባሕር ትከታለች፣ እሳት ላይ ትጥላለች፣ ገደል ትሰዳለች፤ አደገኛ ናት! ... ዕጿን፤ ለመቁረጥ ቢያንስ የሶስት ቀን ዝግጅት ያስፈልጋል።... ፀሎተ ድግምት ሲደረግ፤ የአቆራረጥ ገቢር፣ ለአጋንንት ቀለብ የሚሆን የነጭ ዶሮ ደም መስዋዕት አቅርቦ፣ ቡና፣ እጣን፣ ቆሎ፣ ቂጣና አረቂ... ተይዞ፤ በሥርዓትና በአግባቡ ከተቆረጠች፤ ለማንኛውም ሕመም ፈውስ አላት።*

በማለት አስረድተዋል። ከዚህ በላይ የቀረቡ የመስክ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ዕፅዋት፤ በሽታን ወይም አጋንንትን የመሸከምና

የማስተላለፍ ኃይል እንዳላቸው፤ በአንጻሩ የድኅነትና የፈውስ ምክንያት እንደሆኑ ተጠቁሟል። ለጋኔል፣ ለሰይጣን፣ ለቆሌና ለዛር መኖሪያና መስፈሪያ የተመረጡ ዕፅዋት በመልካም ሽታቸው፣ በጥሩ መዓዛቸው፣ በጣፋጭ ፍሬያቸው አገልግሎት የሚሰጡ ዛፎች ለአጋንንት መኖሪያ ተስማሚ እንደሆኑ ይነጋራል። ለምን? ሲባል የዛርና የጅን መንፈስ… "ጥሩ ሽታና መዐዛ ስለሚወዱ" ይባላል።

የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች፤ በሰው፣ በአዕዋፍ እና በእንስሳት የሚበሉ፤ ጣፋጭ ይዘት ያላቸው አትክልትና ፍራፍሬ መገኛ ቦታዎች በፍሬያቸው መብሰልና መበስበስ ምክንያት፤ ለባክቴሪያ፣ ለፈንገስ፣ ለቫይረስ እና ለተለያዩ ተሕዋሲያን መራቢያና መኖሪያ መንስኤ እንደሚሆኑ አስረድተዋል። በሂደትም ወቅትና ጊዜ ያለፈባቸው የበሰሉና የበሰበሱ አትክልትና ፍራፍሬዎችን የሚመገቡና የሚጠቀሙ ሰዎች፣ እንስሳትና አዕዋፍ በቀላሉ ለሕመም እንደሚጋለጡ፤ መክረዋል። በተፈጥሯዊ፤ ይዘታቸው ጣፋጭ የሆኑ አትክልትና ፍራፍሬዎች በቀላሉ የመበስበስ፣ ይዘትና ጣዕማቸውን የመቀየር ባሕርይ እንዳላቸው፤ ወቅትና ጊዜያቸውን ጠብቆ ሳይበላሹ መመገብ ተገቢ መሆኑን መክረዋል። የስኳር ጣዕም ያላቸው ጣፋጭ ምግቦችን አዘውትሮ መመገብ የጤና አመጋገብ ልክን በማዛባት ለአጥንት መሳሳት፣ ለሰውነት ውፍረት እና ለተለያዩ በሽታዎች እንደሚዳርግ፤ አቶ እሸቱ ገልጸዋል። በይዘታቸው ጣፋጭና ለስላሳ የሆኑ ምግቦች በአጭር ጊዜ ውስጥ የመሻገት፣ የመበስበስ፣ የመበላሸትና ጣዕማቸውን የመቀየር ኃይል እንዳላቸው፤ ለምግብ መመረዝ፣ ለተቅማጥ፣ ለአንጀት ተስቦ፣ ለታይፎይድ እና ለተለያዩ አካላዊ ሕመም መንስኤ እንደሆኑ፤ ከመስክ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል። የዕፅዋት ጣዕም ባሕርይ፣ ዓይነትና ባህላዊ ምደባ ማሕቀፍ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ምስል 2፡- *የዕፅዋት ጣዕም ባሕርይ፣ ዓይነት እና ባህላዊ ምደባ ማሕቀፍ*




*ምንጭ፡- የባህል ሐኪሞች ምድብ፣ በጥናቱ አቅራቢ ተዘጋጅቶ የቀረበ የካቲት/2011 ዓ.ም*

በባህል ሕክምና ዕውቀት፣ ሥርዓትና ተግባር መሰረታዊ የዕፅዋት ጣዕም ዓይነቶች፤ ጣፍጭ፣ መራራ፣ ለስላሳና ጎምዛዛ/አቃጣይ ይዘቶች ናቸው። ከእነዚህ ይዘቶች መካከል፤ ጣፋጭና ለስላሳ ጣዕም እና ጠረን ያላቸው ዕፅዋትና ምግቦች ለአጋንንት፣ ለዛር፣ ለቡዳና ለጅን መንፈስ ማደሪያ በመሆን፤ ለሕመም አጋላጭና ምክንያት ተደርገው ይታሰባሉ። በተቃራኒው መራራ፣ ጎምዛዛ፣ ኮምጣጣ፣ አቃጣይ ይዘትና ጣዕም ያላቸው ዕፅዋት ርኩስ መንፈስ ለማናገር፣ ለመጥራት፣ ለማስለፍለፍ፣ ለማስወጣት፣ ለመገዘት፣ ከአጋንንት ለማላቀቅና ከሕመም ለመፈወስ ግብዓት ሆነው በዋናነት ይቀርባሉ። የአካባቢው ማኅበረሰብም በይዘታቸውና በጣዕማቸው መራራ፣ ጎምዛዛና አቃጣይ (ጌሾ፣ ሎሚ፣ ብሳና፣ ጉሎ፣ ግራዋ፣ ሰንሰል፣ ቃጫ፣ ቅንጭብ…) ጣዕም ያላቸውን ዕፅዋት፤ በግቢያቸው መትከልና አጥር ማድረግ፣ ማቅረብና መንከባከብ፤ ርኩስ መንፈስን ለማራቅ፣ ከሕመም ለመፈወስ ምርጫቸው እንደሆኑ፤ መገንዘብ ተችሏል። ጠቅለል በአለመልኩ፤ ጣፍጭ ይዘት እና ጣዕም ያላቸው የዕፅዋት ፍራፍሬና አትክልት፣ ምግብና መጠጦች በአጭር ጊዜ ውስጥ ጣዕማቸውን የመቀየር፣ ይዘታቸውን የመለወጥ፣ የመበስበስ ባሕርይ እንዳላቸው፤ አካባቢን የመበከል ኃይላቸው ከፍተኛ እንደሆነ፤ ለጉንፋን፣ ለአስም፣ ለምግብ መመረዝ፣ ለአንጀት ተስቦ፣ ለአካላዊ ቁስለት፤… መንስኤ እንደሆኑ፤ ከቀረበው ይዘት መገንዘብ ተችሏል።

በማኅበረሰቡ እምነትና እሳቤ ሥጋ በል፣ ተናካሽ፣ ተናዳፉ፣ ቆንጣጭና ደም መጣጭ፤ ባሕርይ እና ጠባይ ያላቸው እንስሳት አጋንንት ተሸክመው "ይዞራሉ፣ ይጠራሉ፣ ይበራሉ"፤ ይባላል። ከነዚህ በተቃራኒ ሣር እና ቅጠል በል እንስሳትን በማቅረብ፤ ለምግብ (የቀንድ ከብት) እና ለሥራ (የጋማ ከብት) አገልግሎት ይጠቀማሉ። ሥጋ በል እንስሳት አጋንንት ተሸካሚ፤ ሣርና ቅጠል በል እንስሳት "ቅዱስ" ተደርገው ይቆጠራሉ (ሸሆናቸው ድፍንና የማያመነዥጉ ከጋማ እንስሳት ውጪ) ለምግብ አገልግሎት ይውላሉ። እንደ ባህል ሐኪሞች መረጃ፤ ጅብ፣ እባብ፣ መዥገር እና በአጠቃላይ ሥጋ በል እና ደም መጣጭ እንስሳት ይብዛም ይነስ፤ አጋንንት ተሸክመው እንደሚኖሩ እና እንደሚዞሩ፤ ከአጋንንት እየታገሉ "ሥጋ ይበላሉ፤ ደም ይመጣሉ፤ ይጠጣሉ" ተብሎ ይታመናል፤ ይተርካል። እነዚህ እንስሳት የለከፉት፣ የቀመሱት፣ የላሱት፣ የረገጡትና ያሸተቱት ምግብና መጠጥ በጋኔል ያስመታል፤ ተብሎ ይፈራል።

ይህ ጥናት በተካሄደበት አካባቢ፤ የምግብ ዝርዝር ምርጫ ውስጥ በዋናነት ከዕፅዋት እና ከዕፅዋት ተመጋቢ እንስሳት ወገን ያሉትን (ሸሆና ክፍትና የሚያመነዥጉ እንስሳትን) ይመረጣሉ፤ በአንፃሩ ሥጋ ተመጋቢ እንስሳት በሃይማኖት የማይፈቀዱ፤ በምግብ ዝርዝር ሥርዓት ውስጥ

የማይካተቱ፤ መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል። እንደ ማኅበረሰቡ እሳቤና ፍልስፍና፤ ለባክቴሪያ፣ ለቫይረስ፣ ለፈንገስ፤… የቀረቡና በዋናነት ተጋላጭ የሚባሉ እንስሳትን በማራቅ፤ ዕፅዋት ተመጋቢ የሆኑትን በማቅረብና በማላመድ ለምግብና ለሥራ መጠቀማቸው፤ ከሥጋ በል እንስሳት ጋር ያላቸውን ቅርበት፣ ተራክቦ፣ ንክኪ እና ይዘት መገደብና ማራቃቸው፤ አንጻራዊ በሆነ መልኩ ማኅበራዊ ጤናቸውን ለመጠበቅ፤ አስተዋጽኦ እንዳለው መገንዘብ ተችሏል።

## በቆሻሻ የሚኖሩ፣ "በወንዝ" የሰፈሩ አጋንንት

እንደባህል ሐኪሞች እና ማኅበረሰቡ እሳቤ፤ የአጋንንት መኖሪያ አካባቢና መከሰቻ ዐውዶች ከሚባሉ ይዘቶች መካከል፤ ቆሻሻ መድፊያና መጣያ ቦታ፣ ብስባሽ ያለበት አካባቢ፣ ሞተው በሚገኙ እንስሳት (አህያ፣ ፈረስ እና የዱር እንስሳት)፣ ምግብና መጠጥ፣ ከብት የታረደበትና ደም የፈሰሰበት ቦታ መለከፍያ መንገዶች እንደሆኑ፤ በማኅበረሰቡ ይታመናል። የአጋንንት አለቃ፣ ታዛዥ፣ ውላጅና ጭፍራ የሆኑ "የጋኔል እና ጅን" ዘሮች በቆሻሻ እና በወንዝ (በባሕር) አካባቢ ሰፍረው፤ እንደሰው የሚሰሩ፣ የሚበሉ፣ የሚጠጡ፣ ተዋልደው የሚኖሩ፤ የዚህ ዓለም ግልባጭ ሕይወት በነሱም እንዳለ፤ የራሳቸው ግዛት፣ ቦታና ሥልጣን እንዳላቸው ይታሰባል። በቆሻሻ፣ በብስባሽ፣ "በጥንብ" [በሞቱ እንስሳት አካላይ ሰፍረው የሚገኙ] እና በመሬት ግዛትና ቦታ ላይ "ወረው" የሚኖሩ፤ ሥልጣንና ኃይል ያላቸው "የመሬት ጋኔል" ተብለው እንደሚጠሩ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል።

እነዚህ አጋንንት "ልቡሳነ ሥጋ" የነበሩ፤ እንደሰው ሰርተው፣ ለፍተው፣ ምግብ በልተው እንደሚኖሩ፤ ከሥራ ተመልሰው በእኩለ ቀንና ሌሊት (ከአምስት እስከ ዘጠኝ ሠዓት ባለው ጊዜ) ቤታቸውን ገብተው ቡና አፍልተውና ጠጥተው እንደሚተኙ፤ በማኅበረሰቡ ይነገራል። አጋንንት ይኖሩበታል በሚባል ቦታ መንቀሳቀስ "ያስለክፋል፣ በጋኔል ያስመታል"፤ ይባላል። ጋኔል፤ "ፈጣን፣ ቁጡና አደገኛ" ስለሆነ በቁም ይጥላል፣ "አናት" (እራስ) ያዞራል፣ ሆድ ይነፋል፣ ተቅማጥ ይለቃል፣ ብርድ ብርድ ይላል፣ በመላው የሰውነት "ጅስም" [በመላ ሰውነት ይሰራጫሉ] ይበተናል፤ ይሰራጫል፤ ተብሎ ይታሰባል። በተለይ የመቃብር ቦታ ጠባቂው ጋኔል "ሞርሞሪዎን" በእኩለ ቀንና ሌሊት የመቃብር ቦታ የረገጡ ሰዎች በዚህ ጋኔል እንደሚመቱ፤ "የአካል ቁስለት ያለባቸው" እና ነፍሰጡር እናቶች በአካባቢው ቢደርሱ ቁስሉ ይብሳል፤ ነፍሰጡር እናቶችን "ይጣላል" [ለሕመም ይዳርጋል] ተብሎ ይፈራል።

ከማኅበረሰቡ አባላት፤ መቃብር፣ ሰርግ፣ ገበያ ቦታ… ደርሶ የተመለሰ፤ "ፀሐይ ላይ ቆይቶ" የመጣ ሰው፤ "ሕመምተኛ አይጠይቅም፤ ለታማሚው 'ጥላ' ይሆናል" [ሕመሙን ይቀሰቅሣል፤ እንዲባባስ ወይም

እንዲያገረሽ ያደርገዋል] ተብሎ የታመናል፡፡ በርቀት ቆመው፤ ወደ ቤት ሳይገቡ ሰላምታ አቅርበው፤ "ምሕረት ይላክልህ!" ብለው፤ ከማለፍ ውጪ በአካል ቀርበው፣ በእጅ ዳብሰው ሕመምተኛን አይጠይቁም፤ ይባላል፡፡ ለምን?፤ በመቃብር ቦታ፣ በገበያና በፀሐይ አካባቢ ውለው የሚመጡ ግለሰቦች፤ ዶሮና እንስሳት በተለያየ የሰውነት አካላቸው አጋንንት (አቧራና ቆሻሻ) ይዘውና ተሸክመው እንደሚመጡ ይገመታል፡፡ ይህ ተግባር ለሕመም መባባስና ማገርሸት ምክንያት እንደሚሆን፤ ከረጅም የሕይወት ተመክሮ፣ ፍልስፍና፣ እሳቤና ተግባር እንደተማሩት፤ የታካሚን ጤና መጠበቂያ ሥርዓት እንደገነቡ፤ መገንዘብ ተችሏል፡፡

በዘመናዊ ሕክምና የሕመም መንስኤ፤ ባክቴሪያ፣ ቫይረስ፣ ፈንገስ፣ ጥገኛ ትላትል እንደሆኑ በዋናነት፤ ተጠቁሟል፡፡ መተላለፊያ መንገዳቸው በትንፋሽ፣ በተበከለ ውኃ እና ምግብ፣ ንጽህናው ባልተጠበቀ መኖሪያ ቤትና ሽንት ቤት፣ በባክቴሪያና በፈንገስ የሚከሰቱ የሰውነት ቁስለትን፤ … ይመለከታል፡፡ ቆሻሻ የሚጣልበት (የቡና፣ የአረቄ፣ የጠጅና ጠላ አተላ የሚደፋበት) ማንኛውም አካባቢ፤ ለፀሐይ ሙቀት ተጋላጭ ሲሆን፤ ከፍተኛ የሆነ የመብላላት ወይም “የፈርሜንቴሽን ፕሮሰስ” ሥርዓት ይካሄዳል፤ በሙቀትና በንፋስ እየታገዙ ባክቴሪያዎች (ታይፎይድ፣ የአንጀት ተስቦ፣ ቲቢ፣ ትኩሳት፣ ኮሌራ…) አካባቢያቸውን በመበከል፤ በየቦታው ሲሰራጩ ለታይፎይድ፣ ለምግብና መጠጥ መመረዝ ምክንያት እንደሚሆኑ አስረድተዋል፡፡

ከዚህ አንጻር የማኅበረሰቡ እና የባህል ሐኪሞች ባህላዊ ዕውቀትና ልማድ፣ እምነትና ተግባር፣ ልምድና ሥርዓት፣ እለታዊ እንቅስቃሴዎች፣ ማኅበራዊ መስተጋብር፣ የዘመንና የሕይወት ተመክሮ መነሻ በማድረግ፤ የሰው ልጅ በእኩለ ቀን በቆሻሻ ቦታ፣ በወንዝ ዳርቻ፣ በአድባር እና በመቃብር ቦታዎች መንሳቀስ ለሕመም መንስኤ፤ ለሞት ምክንያት እንደሚሆን በማኅበረሰቡ ልማድ ተለይቷል፡፡ በአንጻሩ የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎችም በማንኛውም ሠዓት ወይም እኩለ ቀን በቆሻሻ ቦታ መገኘት፣ መንቀሳቀስ ወይም በአቅራቢያ መኖር፤ ለሕመምና ለሞት መነሻ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በማኅበረሰቡ እሳቤ ቆሻሻ ቦታና ወራጅ ወንዝ የአጋንንት መገኛ ተደርገው ይታሰባሉ፤ አጋንንት ረቂቅ፣ በቆሻሻ ቦታ የሚኖሩ፤ በእኩለ ቀን ሰውና እንስሳት እንደሚለክፉ፤ ተጠቁሟል፡፡ በዘመናዊ ሕክምናም ቢሆን በዓይን በማይታዩ "ረቂቅ ተሕዋሲያን" [ባክቴሪያ፣ ቫይረስ፣ ፈንገስ፤] አማይኝነት፤ በዐየር እየተገፉ፣ በሙቀት እየተነሱ፣ በልብስ፣ በእግርና በእንስሳት ንክኪ እየተዛመቱ፣ በመመገቢያ እቃዎች እና መሰል ቦታ በመባዛትና በመራባት [ይስት ወይም ሽጋታን ልብ ይሏል]፤ ለሕመም እንደሚዳርጉ ተጠቁሟል፡፡ በሁለቱም ዘርፎች ያለው አተያይ፣ እሳቤና ተግባር

ተቀራራቢ ቢሆንም መሰረታቸው፣ እድገትና ምንጫቸው፣ የባህልና የሣይንስ እሳቤ እና ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ግቡና ተግባሩ ተዛማጅ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

## በደም፣ ምግብና መጠጥ የሚነሱ አጋንንት

በደቡብ ጎንደር ማኅበረሰብ እምነትና እሳቤ፤ ደም የአካል እና የነፍስ ድልድይ፣ የድሕነትና የምህረት መንገድ፣ የዕርቅ ማፅኛ እና የፈውስ ምክንያት በመሆን ይቀርባል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የመርገምት ተምሳሌት (የሄዋን የወር አበባ)፣ የአጋንንት ማረፊያ፣ የሕመም መነሻ እና የሞት ምክንያት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ "ከእንስሳት እርድ የሚፈስ ደም አይቀመስም/አይጠጣም" ይባላል፤ ለምን? ሲባል "ሕይወት አለው" ተብሎ ይታመናል፡፡

ደም፤ የአካልና የነፍስ መጋጠሚያ፣ የሕይወት ድልድይ፣ የምህረት መንገድ፣ የዕርቅ ማፅኛ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ከሃይማኖታዊ እሳቤ፤ አካላዊ ሥጋን ከሚያስገኙ ባሕርያት ነፋስ፣ እሳት፣ ዉኃ እና መሬት የተሰራ የሕይወት መሰረት፣ የእስትንፋስ አካል ተደርጎ ይታመናል፡፡ ሰው ተጣልቶ ደም ቢፈስ፣ ሕይወት ቢጠፋ ማስታረቂያ፣ ማስማሚያ፣ ማግባቢያና የዕርቅ ማፅኛ፣ መገዘቻ ስልትና መንገድ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ "የሽማግሌ ቃልና ግዝት ባፈርስ.. ደሜ ይፍሰስ፤… ብከዳ፤ የቆምኩበት መሬት ይክዳኝ!..." እየተባለ መሃላ ይደረጋል፡፡


በጠና ታሞ በአልጋ የዋለን ሰው ከሕመም ለመፈወስ፣ ስቃዩን ለመቀነስ በሽታውን ወደ ሌላ አካል ለማስተላለፍ፤ "መጸሐፍ ተገልጦ"፣ ኮከብ ይቆጠራል፤ በተቆጠረውና በተጠቆመው ኮከብ መሰረት እየታገዙ (እየተመሩ)፤ የዶሮ፣ የበግ፣ የፍየል መልክ፣ ዓይነት፣ መጠን፣ የጭዳ ልክና ሥርዓት ይነገራል/ይዘጋጃል፡፡ ለዓብነት ያህል፡- ታሞ በአልጋ ለከረመና ለዋለ ሰው፤ ቡና ተፈልቶ፣ ቆሎ፣ ቂጣ፣… ተዘጋጅቶ፤ የታማሚው ሰው ኮከብ፣ ዘመን፣ ወር እና ባሕርይ ተለይቶ ሥርዓቱ ይጀመራል፡፡ "ነጭ የዶሮ ጫጩት ገዝተህ በራስህ ላይ ሶስት ጊዜ አዙረህ ጣል"፤ ለኮከቡ ባሕርይ የሚመጥን ድግምት እየተነበበና እየተደገመ የተመረጠችው ጫጩት በእጅ ተይዛ በታማሚው ሰውነት ላይ ሶስት ጊዜ በማዞርና በማሽከርከር በግቢ ውስጥ መልቀቅን ይመለከታል፡፡ በግቢ የተለቀቀችው ጫጩት ወዲያው ከሞተች በሽታው ለቆ እንደሄደ፤ ይታሰባል፡፡ እያደገች ከሄደች እና ሕመምተኛው ከዳነ የታማሚው ሰው ኮከብ ማረፊያ፣ "ከአጋንንት ጠባቂና ገድ" ተደርጋ ስለምትቆጠር መሸጥ፣ መለወጥና ማረድ እንደማይቻል፤ የመስክ መረጃዎች ገልጸዋል፡፡

በዚህ ጥናት ተተኳሪ ማኅበረሰብ እምነትና እሳቤ "ደም" የመለከፊያ ምክንያት ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ደም፤ ለሕመም መነሻ፣ ለአጋንንት

ማረፊያ፣ መኖሪያ፣ ማቋደሻ ሆኖ ሲቀርብ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የደም መስዋዕት፤ ለምህረት፣ ለፈውስና ለጤና ተብሎ ተግባራዊ ይደረጋል።

ምግብና መጠጥ በአግባቡ ካልተያዙ፤ በማንኛውም ቦታ ቢበሉና ቢጠጡ በአጋንንት ያስመታሉ፤ ለምች ያጋልጣሉ፣ ለክፉ ዓይን (ለቡዳ) ይዳርጋሉ፣ ለሕመም መንስኤ ይሆናሉ፤ ተብሎ ይፈራል። ለምን? ሲባል ከተፈጥሯዊ ባሕርያቸው ተለይተው ሲገኙ ኃይልና ተግባራቸውን በመሳት፤ ገቢራቸውን በመዘንጋት የአጋንንት ማደሪያ ይሆናሉ፤ ተብሎ ይታመናል። በሰው ፊትና በማንኛውም ቦታ የማይበሉና የማይጠጡ፤ ለሕመም አጋላጭ ከሚባሉ ዐውድና ምክንያቶች መካከል ከምግብ (አትክልትና ፍራፍሬ፤ ቅባትና ሥጋ ነክ ይዘት ያላቸው)፤ ከመጠጥ (ወተት እና በቀላሉ የሚበላሹ ጣፋጭ ጣዕም ያላቸው) በዋናነት ይጠቀሳሉ። ለሕመም አጋላጭ፣ አስጠቂ፣ መነሻ የሚባሉ ምግብና መጠጦች በአጭር ጊዜ ውስጥ ይዘታቸውን፣ ባሕርያቸውን፣ ጣዕምና ቃናቸውን በመለወጥ ለሕመም መንስኤ እንደሚሆኑ የሕክምና ባለሙያዎች ይመክራሉ። በአጠቃላይ የመስክ መረጃዎች ጠቅለል በአለ መልኩ ሲታዩ፤ የዐየር ጋኔል ለአዕምሮ መሰወር፣ ለዓይን መጥፋት እና ለፀሐይ ጨረር "ዉጋት" በመዳረግ፤ የመሬት ጋኔል የፊት አካልን በማጣመም እና ለብርድ ሕመም መንስኤ በመሆን፤ የዛር አጋንንት አዕምሮን እና መራቢያ አካልን ማድከምና ሥርዓት ማዛባት፤ የቡዳ መንፈስ፤ በደም፣ በምግብ፣ በመጠጥ ምክንያት በደም ሥር በመዘዋወር ሰውነትን በማንቀጥቀጥና በማዛል አቋምን ማሳት፤ የጅን መንፈስ ደግሞ በወንዝ አካባቢና ዉኃ ላይ ሰፍረው ለዉኃ ልክፍት፣ ለአካላዊ ቁስልና ለሆድ ሕመም በመዳረግ ጉዳት እንደሚያደርሱ ይታሰባል። ከዚህ አንጻር፤ የሕመም መንስኤ የሚባሉ "የአጋንንት ዓይነቶች" የትኛውን የሰውነት አካልና ክፍል በዋናነት እንደሚያጠቁ በሚከተለው ምስለ መዋቅር፤ ተጠቁሟል።

ምስል 3፡- *የሕመም መንስኤ የሚባሉ አጋንንት በዋናነት የሚያጠቁት የሰውነት አካል ክፍል*




*ምንጭ፡- የባህል ሐኪሞች፤ በጥናት አቅራቢው ተዘጋጅቶ የቀረበ ምስለ መዋቅር፤ የሰውነት አካላዊ መዋቅር (*www.http;//thumbs.human-Body-System-chart-52821831.jpg *)።*

## በባህል ሕክምና ሁነትና ሂደት አዎንታዊና አሉታዊ ተግባራት

በደቡብ ጎንደር ዞን የሚኖሩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ለባህል ሕክምና አገልግሎት በአብዛኛው አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ከባህል ሐኪሞች፣ ከአካባቢው ማኅበረሰብና ከታካሚዎች የተገኙ የመስክ መረጃዎች አረጋግጠዋል። የባህል ሐኪሞች በየአካባቢው መገኘትና ተደራሽ መሆናቸው፤ በማኅበረሰቡ ተቀባይነትን ማግኘታቸው፤ በውለታ፣ በቀላል ዋጋና ምስጋና አገልግሎት መስጠታቸው፤ ሥነ ልቡናዊ ድጋፍ ማድረጋቸው፤ የሕክምና ዘርፉን ተመራጭ እንዳደረገው ጥናቱ አስረድቷል። የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች ደግሞ የባህል ሕክምና ዘርፉ በማኅበረሰቡ የተመረጠ ቢሆንም የሚሰጡት አገልግሎት በሳይንስ ለማረጋገጥ የሚያዳግት፣ ምክንያታዊ መርህ ላይ ያልተመሰረተ፤ በግለሰብ ዕውቀትና ልምድ ላይ የተንጠለጠለ እንደሆነ ገልፀዋል። የበሽታ መንስኤ፣ መለያና ምርመራ ዘዴዎቻቸው ከረጅም ጊዜ ልማድ፣ ልምምድ እና ተግባር የተገኙ ቢሆኑም የበሽታ ዓይነቶችን፤ ብዛትና ተመሳስሎን በውል ለመለየት እንደሚቸገሩ የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች ጠቁመዋል። የተወሰኑ የባህል ሐኪሞች ወደ ዘመናዊ ሕክምና ሕሙማንን በመላክ የበሽታቸውን ዓይነት በምርመራ እንደሚያረጋግጡ፤ ዘመኑ እየተለወጠ፣ የበሽታው ዓይነት እየጨመረ ሲሄድ፤ ወቅታዊ ሥልጠና በጤና ቢሮ አስተባባሪነት ቢሰጣቸው፤ የህክምና ቁስና የሕግ ድጋፍ ቢኖራቸው፤ ስለንጽሕና፣ ስለጤና እና ስለሕመም ጠባይ አጫጭር ስልጠና ቢሰጣቸው፤ የባህል የሕክምና ዘርፉ እንደሚለማ የባህል ሐኪሞች አስረድተዋል። ከዚህ አንጻር በማኅበረሰቡና በባህል ሐኪሞች የሕክምና ዘርፉ ተቀባይነት ያለው ሲሆን በዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች ደግሞ ለተወሰኑ በሽታዎች የሚሰጠው ሕክምና ተዓማኒነት እና ተቀባይነት እንደሌለው፤ ጥናቱ ጠቁሟል።

## ማጠቃለያና ይሁንታ

ይህ ጥናት *"በባህል ሕክምና ዕውቀት የሕመም መንስኤ እና የምርመራ ዘዴዎች ትንተና በደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ"* በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን ዓይነታዊ የምርምር ይዘትን በመከተል የትርጓሜ ንድፈ ሃሳብ (Interpretive theory) አካል በሆኑት፤ በሥነ ዕውቀት (Epistemology) እና ማኅበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ (Social Constructionist Theory) እና በሕዝባዊ የሕመም መንስኤ ንድፈ ሃሳቦችን (Lay theories of illness Causation) መሰረት በማድረግ፤ የመስክ መረጃዎችን ከባህል-ተኮር ማብራሪያ ሞዴል (Culture-Centered Explanatory Model) እና ከተፈጥሮ ባሕርይ ሞዴል ምልከታና አንፃር በማደራጀት ፈትሿል። እነዚህ መረጃዎች በገላጭ፣ በይዘት እና ትርጓሜ (Interpretation) ስልት ተተንትነው ቀርበዋል። የጥናቱን ዝርዝር ዓላማዎችና ትንታኔ መነሻ በማድረግ ከሚከተሉት ማጠቃለያ ነጥቦች ላይ ለመድረስ ተችሏል።

እንደ ደቡብ ጎንደር ዞን ማኅበረሰብ (የባህል ሐኪሞች) እሳቤ የሕመም መንስኤ አጋንንት እንደሆኑ ይታመናል። እነዚህ አጋንንት በዋናነት፤ ጅን፣ ዛር፣ ቡዳ፣ የመሬትና የዐየር ጋኔል በመባል እንደሚጠሩና በየትኛው የሰውነት አካልና ክፍል ላይ እንደሚከሰቱ ጥናቱ ጠቁሟል። በሁለተኛ ደረጃ የዚህ ጥናት ትኩረት፤ በባህል ሕክምና ዕውቀት የበሽታ መለያና የምርመራ ዘዴዎች ምን

ዓይነት ተግባርና ይዘት እንዳላቸው ማብራራት ነበር። በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ዓለማዊ የምርመራ ዘዴዎችን በመጠቀም በአካባቢያቸው የሚከሰቱ የሕመም ዓይነቶችን እንደሚለዩ ጥናቱ አሳይቷል። ዓለማዊ ምርመራን የሚከተሉ የባህል ሐኪሞች እይታዊ፣ ክሊኒካዊ፣ ባዮሎጂካዊ፣ የታካሚን የሕይወት ዳራ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መስተጋብሩን በማጤን የበሽታ ዓይነቶችን እንደሚለዩ፤ የበሽታዎችን ባሕርይ በመከተል፤ ድንገተኛና አጣዳፊ፣ አንቀጥቃጭና አርገብጋቢ፣ አቃጣይና አስለፍላፊ፤ ቆንጣጭና ሰርሳሪ፣ አብራጅና አድካሚ፣ አደንዛዥ እና አወፋሪ የበሽታ ዓይነቶች እንዳሉ፤ ጥናቱ ገልጿል። በመጨረሻም፤ በአካባቢው የሚሰጠው የባህል ሕክምና አገልግሎት ማኅበራዊ ግንኙነትን ለማጠናከር፤ በተመጣጣኝ ዋጋ እና ውለታ የሕክምና አገልግሎት ማግኘታቸው፤ ገንዘብ፣ ጊዜና ጉልበት መቆጠባቸው ከፋይዳውም በተጨማሪ የባህል ሕክምና አገልግሎቱን ተመራጭ እንዳደረገው ጥናቱ አስረድቷል።

## ይሁንታ

በባህላዊና በዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎች መካከል የውይይትና የምክክር መድረክ ቢፈጠር፤ የሙያና የዕውቀት ልውውጥ ቢኖር እና ሁለቱም ባለሙያዎች ተቀናጅተው የሚሰሩበት አጋጣሚ ቢፈጠር ለማኅበረሰቡ ጠቃሚና ተገቢ የሆነ የህክምና አገልግሎት መስጠት ይቻላል የሚል እምነት አለኝ።

ባህላዊ ሕክምና ለማኅበረሰቡ የሚሰጠው ጥቅም የጎላ በመሆኑ በዘርፉ ሰፊ ጥናትና ምርምር ቢደረግ፣ ማኅበረሰቡም ሆነ የሕክምና ባለሙያዎች ከምርምር ስራዎችና ጥናቶች ተጠቃሚ የሚሆኑበት አጋጣሚ ቢመቻች የማኅበረሰቡን ጤና በተሻለ ደረጃ ለማስጠበቅ ዋስትና ይኖረዋል የሚል አመኔታ አለኝ። አንዳንድ ግለሰቦች በባህል ሕክምና ስም በቂ ሙያ፣ ችሎታና ልምድ ሳይኖራቸው እና ቁንጽል "ጥራዝ ነጠቅ" ዕውቀት በመያዝ ለጤና ጠንቅ የሆኑ መድኃኒቶችን አዘጋጅተው በመስጠት ሰዎችን ለከፋ ጉዳትና ሞት እንደሚዳርጉ ጥናቱ ጠቁሟል። ስለሆነም፤ በሕግ የሚጠየቁበት መንገድ እንዳለ ማሳወቅ፣ ተከታታይ ትምህርት መስጠት እና ቁጥጥር ማድረግ ይገባል።

## ማጣቀሻ ምንጮች

መስፍን ፍቃዱ (2002)። *የሃገረሰባዊ መድኃኒቶች ቅመማና ባህላዊ አጠቃቀም በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ* (ያልታተመ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት)። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ።

ማኅሌት ዘነበ (2011)። *ሃገረሰባዊ ሕክምና፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ* (ያልታተመ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት)። ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ባሕር ዳር።

*ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት* (1978)። አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

*ምህረት ዳኘው* (2000)፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ የባህላዊ መድኃኒት አዘገጃጀት፣ አሰጣጥና አጠቃቀም (*ያልታተመ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት*)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፡፡

*ሠናይ* ምስክር (2009)፡፡ *መጽሐፈ አክሲማሮስ ዘቅዱስ ኤጲፋንዮስ* (4ኛ እትም)፡፡ ባሕር ዳር፣ አፍሪካ ፕሪንቲንግ፡፡

ተመስገን በየነ (2003)፡፡ በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ በግሼ ወረዳ (*ያልታተመ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት*)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ፡፡

አሰፋ ባልቻ (2008)፡፡ የኢትዮጵያ ባሕላዊ መድኃኒትና ሕክምና የምዕተ ዓመት ጉዞ፡፡ አዲስ አበባ፣ በደራሲው የታተመ፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (1948)፡፡ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ዐቢዩ አስማማው (2010)፡፡ የቦሮ ሽናሻ ብሔረሰብ ሃገረሰባዊ መድኃኒት ምንጩ፤ ተስተላልፎውና ገቢሩ (*ያልታተመ ለፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ ጥናት ማሟያ የቀረበ*)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፡፡

ዓለማየሁ ዘሪሁን (2000)፡፡ የኑዌር ማኅበረሰብ የባህል ህክምና እውቀት አመለካከት፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ (*ያልታተመ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት*)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፡፡

የሊቦ ከምከም ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት *ሪፖርት* (2010)፡፡ የሊቦ ከምከም ወረዳ ማኅበረ-ባህላዊ ዳራ፤ ሊቦ ከምከም (*ያልታተመ*)፡፡

የኢትዮጵያ *መጽሐፍ ቅዱስ* ማሕበር (1980)፡፡ *መጽሐፍ ቅዱስ፤ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት*፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (1993)፡፡ *አማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

የደቡብ ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ (2007፡፡ የደቡብ ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም ዕሴቶች፤ ደቡብ ጎንደር (*ያልታተመ*)፡፡

ይሁኔ አየለ (2010)፡፡ *ሙሉ ጤናን ፍለጋ*፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

*ፈቃዱ ፋ*ላስ (2002)፡፡ *የኢትዮጵያ የባህል መድኃኒት በሳይንሳዊ አቀራረብ፤ የመድኃኒት ዕፅዋት*፡፡ አሜሪካ፣ (አሳታሚ አልተገለፀም)፡፡

ፍቅርተ ማቴዎስ (2009)፡፡ ከዕፅዋት የሚገኙ ሃገረሰባዊ መድኃኒቶች ዕውቀት፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ በከምባታ ብሔረሰብ (*ያልታተመ ለኤም.ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት*)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፡፡

Abraraw Tesfaye. (1993). Traditional Medicine in an urban center, belief and practices፡ The case of Dessie Town, North Ethiopia (Unpublished master's thesis). Addis Ababa University: Addis Ababa.

Alemayehu Moges. (1984). Traditional Ethiopian medicines. *Institute of Ethiopian Studies*; *Eighth International Conferences of Ethiopian Studies.* Addis Ababa University, Addis Ababa.

Assefa Balcha. (1992). Traditional medicine in Wollo: Nature and history (Unpublished master's thesis). Addis Ababa University, Addis Ababa.

Bauman, R. (1983). The field study of folklore in context. In R. M. Dorson (Ed.). *Handbook of American folklore* (pp. 362-368). Bloomington: Indiana University Press,

Bauman, R. (1986). *Story, performance, and event; Contextual studies of oral narratives*. New York: Cambridge University Press.

Ben-Amos, D. (1975). Folklore in African society. *Research in African Literatures*, *l6*(2), 165-198.

Berger, P. &, Luckman, N. (1966). *The social construction of reality: A treatise in the sociology of knowledge.* New York:Penguin Books

Black, W. (1983). *Folk medicine: A chapter in the history of culture.* London: Folklore Society.

Blaxter, L.; Hughes, C., &, Tight, M. (2006). *How to research.* (3rded). England: Open University Press.

Brady, E.(2001). *Healing logics: Culture and medicine in modern health belief systems.* Utah: Utah State University Press.

Chavunduka, G. (1994). *Traditional medicine in modern Zimbabwe.* Zimbabwe: University of Zimbabwe Publications.

Creswell, J.(2014). *Research design: qualitative, quantitative, and mixed methods approach* (4th ed). Thousand Oaks, CA: SAGE.

Dawit Abebe. (1986). Traditional medicine in Ethiopia: The attempts being made to promote it for effective and better utilization. *SINET Ethiop J Sci, 9,* 61-69.

Dawson, C.(2009). *Introduction to research methods: A practical guide for anyone understanding a research project* (4th ed.). Oxford: How to Books.

Fekadu Fullas. (2001). *Ethiopian traditional medicine: Common medicinal plants in perspective*. Sioux City Lowa: St. Luke's Regional Medical Center.

Geertz, C. (1973). *The Interpretation of Culture: Selected Essay*s. New York: Basic Books Publishing.

Good, C.(1987). *Ethno-medical system in Africa: Patterns of traditional medicine in rural and urban Kenya.* New York: The Guilford Press.

Greco, J.(2001). Virtues and rules in epistemology. In A. Fairweather & L. Zagzebski (eds.). *Virtue epistemology: Essays on epistemic vertue and responsibility*. New York; Oxford University Press.

Hammersley, M, &, Atkinson, P.(2007). *Ethnography principles in practice (*3rd ed). London: Routledge.

Helman, C.(1984). *Culture, health and Illness.* Bristol-London-Boston: John Wrighit and sons Ltd..

Hufford, J. (1986). Folk Healers. In R.M. Dorson (ed.), *Handbook of American folklore*.( pp.306-313). Bloomington: Indian University Press:

Hurreize, S.(2006). *Studies in African applied folklore.* Khartoum: Institute of of African and Asian Studies, University of Khartoum.

Kannon, B.(2004). Integration of traditional medicine with modern medicine. In Urga. K, Assefa. A, & Guta. M (eds). *Traditional Medicine in Ethiopia.* Addis Ababa, Ethiopian Health and Nutrition Research Institute, (2004): PP.32-38.

Kloos, J.(1973). A historical overview of traditional medicine practices and policy in Ethiopia. *Ethiopian Journal of Health Development, 20*(2), 127-134.

Kokwaro, O.(1976). *Medicinal Plants of East Africa*. Kampala: East Africa Press.

Konadu, K.(2007). Indigenous medicine and knowledge in African society. New York and London: Taylor and Francis Group PLC.

Kothari, C.(2004). *Research methodology: Methods and techniques.* India: New Age International Limited Publisher.

Leung, L.(2010). Traditional Chinese medicine: A beginner's Guide. *InnovAiT* 4(1): 49-54. DOI:10.1093/innovait/inq115.

Martin, D. (2003). *Traditional medicine in contemporary contexts: Protecting and respecting indigenous knowledge and medicine*. Ottwa: National Aboriginal Health Organization.

Mekonnen Bishaw. (1988). Integrating indigenous and cosmopolitan medicine in Ethiopia [Doctoral dissertation]. University of Carbondale, Southern Illinois, U.S.A.

Mekonnen Meressa.(2010). Indigenous medicine, beliefs and practices among the Kunama in Sheraro, Tigray [Unpublished master's thesis]. Addis Ababa University.

Mekonen Workineh.(2008). The attitude of traditional practitioners, biomedical workers and the public towards traditional medicines with particular reference to rabies healers in West Gojjam [Unpublished master's thesis]. Addis Ababa University.

Messeret Sissay.(1996). The role of health professionals in the development of traditional medicine in Ethiopia. In Dawit Abebe (ed), *Development and utilization of herbal remedies in ethiopia*.(pp. 15-19). Addis Ababa, Ethiopian Health and Nutrition Research Institute.

Mirgissa Kaba.(1993). Indigenous medical beliefs and practices among the Oromo of Illubabor [Unpublished master's thesis]. Addis Ababa University.

Molvaer, R. K.(1987). Medical anthropology: Topics of relevance for health workers and students of health in Ethiopia. Addis Ababa: UNICEF/ Ministry of Health.

Murdock, G. P.(1980). *Theories of illness: A world survey*. Pittsburgh; University of Pittsburgh Press.

Pankhurst, R.(1965). "An Historical Examination of Traditional Ethiopian Medicine and Surgery." Publisher not identified.

Pankhurst, R. (1990). An Introduction to the Medical History of Ethiopia; with a Post Script by Asrat Woldeyes. Red Sea. New Jeresy.

Pankhurst, R.(2005). Traditional Ethiopian Knowledge of Medicine and Surgery: An Introduction to Sources: Indigenous Knowledge Systems in Ethiopia. *Proceedings of the first national workshop of the Ethiopia chapter of OSSREA*. Addis Ababa: Image Printing Press.

Riddle, J. (2013). Folk tradition and folk medicine: Recognition of drugs in classical antiquity. *Pharmacy in History*, 55 (2/3), 64-87.

Schoemaker, G. (Ed.). (1990). *The emergence of folklore in everyday life: A field guide and source book*. Indiana Universitt: Trickster Press.

Sims, M, & Stephens, M.(2005). *Living folklore: An introduction to the study of people and their traditions*. Logan, Utah: Utah State University.

Sosa, E. (2007). *A Virtue epistemology; Apt belief and reflective knowledge*. *Vol.I*. New York; Oxford University Press.

Sofowora, A.(1982). *Medicinal plants and traditional medicine in Africa*. Hoboken: John Wiley and Sons LTD.

Steiner, R. P. (Ed.). (1986). *Folk medicine: The art and the science.* Washington, D.C.: American Chemical Socieity.

Sutton, M. and Anderson, E.(2010). *Introduction to cultural ecology* ($2^{nd}$ ed.) New York: AltaMira Press.

Tebaber Chanie. (2015). Indigenous medical knowledge and practices: cultural and environmental values of medicinal plants used by the Konso people of South Western Ethiopia. [Unpublished master's thesis, Addis Ababa University].

Teshome Bahire. (2000). Initiation of healers in Ethiopia: A case study. *Journal of Anthropology*, *24* (2), 555–563.

Trostle, J.(2005). *Epidemiology and culture*. New York: Cambridge University Press.

WHO (2002). *WHO Traditional medicine strategy 2002-2005*. Geneva; World Health Organization.

WHO (2007). *WHO international standard terminologies on traditional medicine in the western pacific region*. Geneva: World Health Organization.

Winkelman, M.(2009). *Culture and health applying medical anthropology*. San Francisco; John Wiley and Sons Imprint.

Wondwosen Teshome.(1999*)*. Indigenous medicinal plants used in Ethiopia. *Viennese Ethno medicine News Lette*r, *9* (2), 28-32.

Wondwosen Teshome.(2006).*Medical pluralism in Ethiopia*. Germany: Shaker Verlag.

Yoder, D.(1972). Folk medicine. In R. Dorson (ed.), *Folklore and folk life: An introduction* (pp.190-214). Chicago: University of Chicago Press.

Young, A.(1970). *Medical beliefs and practices of begemder Amhara* [Published doctoral dissertation, University of Pensylvania, Philadelphia].

Young, A. (1976). Internalizing and externalizing medical belief system; An Ethiopian example. *Journal of Social Science and Medicine Department of Anthropology*, *10*, 147-156.

Young, A. (1980). An anthropological perspective on medical knowledge. *The Journal of Medicine and Philosophy*, *5*(2), 102-116.

Zerihun Doda. (2001). Culture, belief and mental illness among the Zay [Unpublished master's thesis, Addis Ababa University, Addis Ababa].